EEA/EEPRI

Ethiopian Economic Association/ Ethiopian Economic
Policy Research Institute
Tel. 251-1- 55 74 59, 251-1 12 80 77
Fax No. 251-1 56 52 52
P.O.Box 34282, A.A Ethiopia:
e-mail: eea@telecom.net .et

EEA/EEPRI

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር/
የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክ ፖሊሲ ምርምር ተቋም

# መልካም አተስዳደር ፤ የኢኮኖሚ ልማት እና የድህነት ቅነሳ ሰነድ

ለድህነት ቅነሳ ስትራተጂ ሰነድ ዝግጅት
ስልጠና የተዘጋጀ

ዶ/ር ሽመልስ ተ/ፃዲቅ

መስከረም 1994 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# ማውጫ


| እርእስት | ገጽ |
| --- | --- |
| I- መግቢያ | 1 |
| II- የዲሞክራሲ ስርዓትና ገጽታው | 3 |
| ዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር | 7 |
| III- መልካም አስተዳደርና የኢኮኖሚ ልማት | 10 |
| መልካም አስ፡ዳደር | 11 |
| የኢኮኖሚ ልማት | 16 |
| በመልካም አስተዳደርና በኢኮኖሚ ልማት መካከል ያለው ግንኙነት | 20 |
| IV. የታዳጊ አገሮች መልካም አስተዳደርና የኢኮኖሚ ልማት ሁኔታ | 22 |
| የኢኮኖሚ ልማት | 24 |
| መልካም አስተዳደር | 28 |
| V- ድህነት በኢትዮጵያ | 34 |
| VI- የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ (PRSP) ዝግጅትና የሕዝብ ተሳትፎ | 39 |
| የድህነት ቅነሳ ስልት መንደርደሪያ ሃሳቦች | 42 |
| የተሳትፎና የትብብር መዋቅር መንደርደሪያ ሃሳብ | 44 |
| የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ (PRSP) ዝግጅትን በተመለከተ | 46 |
| የዚህ ስልት ዝግጅትና የዲሞክራሲ ግንባታ | 52 |

# መልካም አስተዳደር

## I. መግቢያ

ይህ ጽሑፍ በአጠቃላይ የሚመለከተው በዴሞክራሲ፣ በመልካም አስተዳደርና በኢኮኖሚ ልማት መካከል ያለውን ግንኙነት ነው:: በሁለተኛ ደረጃ የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድን (PRSP) አስመልክቶ መልካም አስተዳደርና የኢኮኖሚ ልማት ድህነትን ለመቋቋም በምን መንገድ ይቀናጃሉ የሚለውንም ጥያቄ ለመመለስም ይሞክራል:: ይህም የሚሆነው በኢትዮጵያ አገራዊ ማእቀፍ (frame work or historical context) ውስጥ ነው:: ማለትም የመልካም አስተዳደርን፣ የኢኮኖሚ ልማትና ድህነትን የመቋቋም ጽንሰ ሃሳቦችን ማብራራት ብቻ ሳይሆን እነዚህን በኢትዮጵያ ሁኔታ ውስጥ ማየትም ይፈለጋል:: እነዚህን ጥያቄዎች በአንድ አጠር ባለ ጽሑፍ በሚገባው ደረጃ ለመመለስ አስቸጋሪ ነው:: ምክንያቱም የማኅበራዊ ሳይንስ እውቀቱም የተወሰነ ነው፣ በመሠረቱም የሰውን ልጅ ተግባር እንደ ቁሳቁስ ነገሮች ለማጥናት በቂ ሳይንሳዊ ዘዴም የለ::[1]

ነገር ግን እንደ ሰው ልጅ አጠቃላይ እሴት፣ እንዲሁም የራሳችን የዜጎች ፍላጎት ይኸን ይመስላል ማለት ይቻላል፤ ደሞም በመሠረቱ በዘመናት ያጠረቀምነውን ዕውቀትና ተሞክሮ በማቀናጀት ዴሞክራሲም ሆነ የኢኮኖሚ ልማት ለእራሳችን የምናስገኘው በኑሮ ጥረታችን ነው:: ምክንያቱም ዴሞክራሲ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ልማት በእራሳቸው ከሰው ልጅ ተፈጥሮ ፍላጎትና እሴት ጋር የተሳሰሩ ናቸው:: መሠረታዊ እሴቶቹም፣ አለም በተቀበለው የፈረንሳይ 1789 አብዮት መፈክር አባባል *ነፃነት፣ እኩልነት፣ እና ወንድማማችነት* ናቸው::

ከዚህም በላይ ይኸን ጽሑፍ የማዘጋጀቱን ተግባር ያከበደው ቀጣሪዎቼ ጽሑፉ የሚፈለገው ለማስተማር ስለሆነ ቀለል ባለ ቋንቋና የምትለው ሁሉም ግልጽ እንዲሆን ያስፈልጋል አሉኝ:: እንግዲህ ይታያችሁ በደንብ እውቀቱ የሌለ ነገርን እንደ መጠቀሚያ (manual) የሚያገለግል ጽሑፍ ማዘጋጀት ደሞ ባጣም ይከብዳል፣ አንዳንዴም

---

[1] እንደ ታላቁ የፈረንሳይ ፈላስፋ ሳርትር አባባልም የሰውን ልጅ ነፃነት በሳይንሳዊ ሕግ ወደ ተዋቀረ የኢኮኖሚም ይሁን ሌላ መንስዔ ወይም ምክንያት ደረጃ ማውረድ አይቻልም::

ጥረቱ ቁም ነገሮቹንም በማይሆን መንገድ ያቃልላል::[2] ለራሴ የተሰጠኝን ተግባር፣ በሁለት መንገድ ማቅለል የቻልኩ ይመስለኛል:: አንደኛው እኔም ሆንኩ በዚህ ጽሑፍ የሚማሩትም ኢትዮጵያውያን ነን፣ እንደ ዜጎች ደግሞ ማንኛውም ትልቅ አገራዊ ተግባር ሁላችንንም ያገባናል:: ስለዚህ እኔ ባለኝ አቅም የተቻለኝን አዘጋጅቼ በማቀርበው ጽሑፍ አነሳሽነት ሁላችንም አብረን እንማርበታለን በማለት እራሴን አደፋፈርኩት:: በነገራችን ላይ አገሪቱን ማልማትም ይሁን ማጥፋት እኛው ብንሆን ይሻላል በማለጽ ከተመካከርን ደሞ የምናለማት ይመስለኛል:: ሁለተኛው አሻሚና ንትርክ ያለባቸውን ሃሳቦች ከጠቀስኩኝ በተቻለ መጠን በግርጌ ጥቆማ (foot note) ቦታ ብቻ ለማድረግ እሞክራለሁ:: ማለትም የግርጌ ጥቆማዎች ላይ ሃሳቤን ሳልገታ በደንብም ማብራራት ሳይኖርብኝ አሻሚም ቢሆኑ መባል አለባቸው ብዬ የምገምታቸውን ሃሳቦች ለማቅረብ እጠቀምባቸዋለሁ::

የጽሑፉ አቀራረብ እንደሚከተለው ይሆናል:: በሚቀጥለው ክፍል የመልካም አስተዳደር ጠባይ ከዴሞክራሲ የሚፈልቅ ነው ብሎ በመገመት የዴሞክራሲን ስርዓትና ገጽታ ጽንሰ ሃሳቦች እዘረዝራለሁ:: በሶስተኛው ክፍል ከዴሞክራሲ ገጽታ ሊገኙ የሚችሉትን የመልካም አስተዳደር ጠባይ በመጠቀም ከኢኮኖሚ ልማት ጋር ያላቸው ግንኙነት ምን እንደሚመስል ለማየት ይሞከራል:: እነዚህ ሁለት ምዕራፎች ውስጥ የሚባለው በጥቅሉ ከምዕራባውያን ታሪክ ጋር በማያያዝ የፖለቲካም ሆነ የኢኮኖሚ መሻሻል ምሳሌ (model, ideal type) ሆነው እንዲያገለግሉ ነው:: ከወዲሁ ግልጽ መሆን ያለበት የኛ መልካም አስተዳደርም ሆነ የኢኮኖሚ ልማት የምዕራባውያንን መንገድ ይይዛል፣ እኛም እነሱን አይናችንን ጨፍነን እንከተል ለማለት አይደለም:: እንዲያውም ይህ መሆንም እንደማይቻል አንድ አንድ ቦታ ይገለጻል::

ከዚያ በአራተኛው ክፍል ታዳጊ አገሮች ላይ በማተኮርና ኢትዮጵያን እንደ ምሳሌ በመውሰድ በጥቅሉ ለሶስተኛ አለም አገሮች የመልካም አስተዳደርና የኢኮኖሚ ልማት

---

[2] አንድ እንግሊዝዊ የታሪክ ተመራማሪ አንድ አንድ የልማት ኢኮኖሚ ባለሞያዎችን በማሽሟጠጥ ያለውን እንድጠቅስ ይፈቀድልኝ:: ልክ እንደ ወጥ የመቀቀል ምክር ዓይነት እነሱ የሚሉት "የሚከተሉትን ቅመማት ከሀ እስከ ቀ በዚህ መጠን ወስዳችሁ ደባልቁና ቀቅሉት፣ ውጤቱም እራሱን ወደ ቻለ የዕድገት ጎዳና ያገባችኋል::" "Take the following quantities of ingredients a through n, mix and cook, and the result will be the take-off into self-sustained growth." Eric Hobsbawm, On History. New York: The Free Press, 1997, p. 74.

ተስፋ ምን ይመስላል የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ እሞክራለሁ። የሚቀጥለው ምዕራፍ የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ (PRSP) ላይ ሆኖ ድህነት በኢትዮጵያ ምን እንደሚመስልና በሰነዱ ዝግጅትም ውስጥ የሕዝቡ ተሳትፎ ምን መምሰል እንዳለበት በተከታታይ ሁለት ክፍሎች ሃሳቤን አካፍላለሁ። በመጨረሻው ክፍል እንደ መደምደሚያ የዚህን ስልት ተስፋና ከአገራችንም የዴሞክራሲ ግንባታ ጥረት ጋር እንዴት ሊያያዝ እንደሚችል መንገዱን ለመጠቆም ይሞከራል። በየቦታው ትምህርትና ተሞክሮ እናገኝባቸዋለን የምላቸውን ነጥቦች አስምርባቸዋለሁ።

## II- የዴሞክረሲ ስርዓትና ገጽታው

በብዙዎቻችን ግንዛቤ የመልካም አስተዳደር ጽንሰ ሃሳብ በአሁኑ ዘመን በቀጥታ የመንግሥትና በአገሩም ውስጥ ያሉት የተለያዩ ድርጅቶች ከዴሞክራሲያዊ የአሠራር እና ውሳኔ የመድረስ ዘዴ ጋር የተቆራኘ ነው። ስለዚህ ጠቅለል ባለ መልኩም ቢሆን የዴሞክራሲን ጽንሰ ሃሳብና ገጽታዎቹን ማየት ይጠቅማል። የዴሞክራሲ ስርዓት ግልጽ በሆኑ እምነቶች ወይም ቁም ነገሮች ላይ የተመሠረተ ነው። እነሱም የሚከተሉት ናቸው፤[1]

1. የአንድ ግለሰብ ዜጋ መብት ከማንኛውም ዓይነት የቡድን መብት በላይ መከበር፣
2. የፖለቲካው ኅብረተሰብ በስምምነት ላይ የተገነባ ሆኖ በውስጡ ተፎካካሪ የሆኑ የተለያዩ የፖለቲካ አመለካከቶችን ማቀፍ መቻል፤
3. የፖለቲካ ስልጣን ፉክክሩ ነፃና ርቱእዊ ምርጫ መሆን፤
4. በነዚህ መንገዶች የሚፈጠረው ስርዓትም ዓይነተኛ ጠባይ የተወካይ መንግሥት (representative government) ሆኖ፣ የየራሳቸው መንግስታዊ ሚና፣ የሕግ መወሰኛ፣ የሕግ ተርጓሚ እና የሕግ አስፈጻሚ፣ ባላቸው ነፃ ተቋማት የተገነባ መሆን፣
5. ነፃና ሕጋዊ ፉክክር ያለበት ገበያ መኖር፣

---

[1] ቀጥሎ የተዘረዘሩት የዴሞክራሲ መሠረታዊ ቁም ነገሮች የተወሰዱት ከ John Rawls, Political Liberalism New York: Columbia University Press, 1993, and A Theory of Justice Cambridge, Mass.: Harvard Universsty Press, 1971 ነው።

መልካም አስተዳደር

6. ብዙ ጊዜም የተጎዱና አቅም የሌላቸውን የማኅበረሰቡ አባላት እግምት ውስጥ የማግባትና ርቱእዊ የመሆን ማኅበራዊ ስምምነት አለበት::

እነዚህ ቁም ነገሮች ከሞላ ጎደል ተሟልተው የሚገኙበት ስርዓት ውስጥ ኅብረተሰቡ ብዙ ጊዜም ሰላምና የፖለቲካ መረጋጋት ይኖረዋል። ሌሎች አጋዥና ተዛማጅ ግኝቶችም በግልጽ ይታያሉ:: ከነዚህም ዋናዎቹ የሕግ ልዕልና፣ የዳበረና ነፃ የሆነ የመገናኛ ብዙሃን፣ የሕዝብ ተሳትፎ፣ በተቋማት የተደገፉና የታወቁ ናቸው::

የእንደዚህ አይነት የመንግሥታትም ሆነ የተቋማት አወቃቀር የጀመረበትና አሁንም በአስተማማኝ ሁኔታ የሚገኘው በሰለጠኑት ምዕራባውያን አገሮች ነው:: ይህም ታሪካዊ ግኝት የተገኘባውም ሶስት መቶ ዓመታት በፈጀ የመብት ትግል ነው:: በመጀመርያ በአስራ ስምንተኛው መቶ ዘመን የተገኘው የዜጎች ሕጋዊ (ሲቪል) መብት ነው:: በአውሮፓ የከበርቴ ስርዓት ተመሥርቶ መሳፍንታዊ የገባሩን (የፊዩዳሊዝምን) መዋቅር ሲገረስሰው፣ የጀመረው በአንድ አገር ሰዎች በተለይም በገባሩ፣ ጭሰኛውና በሰራተኛ/አሽከር ላይ የነበረውን የክልል፣ የጉሳ፣ የሙያና መሰሎች በሕጋዊና በመሳፍንቱ ጡንቻ ላይ የተመሠረተ፣ ከፋፍሎና በወሰን አካሉ የተገነባውን ስርዓት በማስወገድ ነበር:: ይኸንንም ለማድረግ የከበርቴው ስርዓት ዋነኛ ጠበቆቹ (the bourgeoisie) በገባሩና በሰራተኛው የትግል አጋርነት አገሩ/ብሔሩ ውስጥ የሚገኙትን ዜጎች ባለው ሕግና ሥልጣን ፊት በእኩልነት እንዲታዩና እንዲስተናገዱ አደረጉ:: በዚህ ታሪካዊ ተግባር መጀመሪያ የተገኘው ዓይነተኛ ውጤት በድንበር የተከለለ፣ የታወቁ ዜጎች የሚኖሩበት በሕግ የታወቀ ልዑላዊ አገር ነው:: በጊዜ ብዛትና በሂደት ለእያንዳንዱ ዜጋ መብት ማስከበርያ፣ ለሰውነቱ ክቡርነት፣ ለንብረቱ ባለቤትነት፣ ለእምነቱ፣ ለእሴቱና አመለካከቱ ነፃነት የሚያረጋግጥበትን ሕጎች፣ የአፈጻጸም ደንቦችና ስነ ስረዓት ፈጥረው እነሱንም የሚተረጉሙና የሚበይኑ ነፃና ገለልተኛ ፍርድ ቤቶችን አቋቋሙ::

ይኸን ሕጋዊ የዜግነት መብት ከተጐናጸፉ በኋላ ሁለት ዓይነተኛ መብቶችን በተከታታይ ለማግኘት መንገዱ ተመቻቸላቸው:: በመቀጠል በአስራ ዘጠነኛው መቶ ዘመን የተገኘው ሁለተኛው ዓይነተኛ የዜግነት መብት ለአስተዳደር ሥልጣንና ቢሮ የመመረጥም

የመምረጥም የፖለቲካ መብት ነው። የዚህ መብት ታሪካዊ ውጤት ዜጎች በግልና በወል የአገሩ ልዑላዊ የስልጣን ምንጭ መሆናቸው መረጋገጡ ነው። በሃያኛው፣ ለኛ በያዝነው፣ ክፍለ ዘመን ደሞ ሶስተኛው ማኅበራዊ መብት ተገኘ። ይህ መብት የአገሩ ኢኮኖሚ በሚችለው መጠን ዜጐች የተደላደለ የኑሮ ዋስትናና በአገራቸውም የስልጣኔ ቅርስ የመሳተፍ ችሎታ እንዲኖራቸው የሚጥር ሲሆን፤ የዚህ ጭብጥ ትርጉም ሥራ ላይ የሚውለው ዜጐች የትምህርትና፣ የጤና አገልግሎት የማግኘትና እንዲሁም ባላቸው አቅም ሠርቶ ለመተዳደር የሚኖራቸው መብት ነው። የዚህም ማኅበራዊ መብት መረጋገጥና አስፈላጊው ዝግጅት ገና በሂደት ላይ ያለ ያላለቀ ትልቅ ተግባር ነው።[4]

እዚህ ላይ የተሰጡት የጊዜ ገደቦች፣ ከዚያ በፊት የእነዚህ መብቶች ጥያቄ አልተነሳም ለማለት አይደለም። በእርግጥ በ13ኛው መቶ ዘመን በእንግሊዞቹ ማግና ካርታ እንዲሁም በፈረንሳይና አሜሪካ አብዮቶች ወቅት፣ ማለትም በ18ኛው መቶ ዘመን፤ የሰው ልጆች መብት ጥንቅር ቀርበው የፖለቲካ ትግል መርህ ሆነው አገልግለዋል። ነገር ግን እነዚህ መብቶች በአሜሪካና በአውሮፓ ኅብረተሰቦች ውስጥ ሰርጸው የገቡትና በተቋማት ታቅፈው ተፈጻሚነት ያገኙት በተባለው ዘመን ነው። ብዙዎቹ መብቶችም እስከያዝነው ዘመን ድረስም ገደብ ነበረባቸው። ለምሳሌ ያህል፡ እንግሊዝ አገር ባለንብረቶችና የዩኒቨርሲቲ ተመራቂዎች እስከ 1945 ዓ. ም. ሁለት እጥፍ የመምረጥ መብት ነበራቸው፤ እስከ 1916 ዓ. ም. ድረስ የአሜሪካ ሴኔተሮች በቀጥታ አይመረጠ-ም ነበር፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ስዊስ አገር ሴቶች የመምረጥ መብት አልነበራቸውም። ዋነው ቁም ነገር፣ በዚህ የትግል ታሪካቸው የተጎናጸፉት ስርአት ያለው፣ ሕጋዊ የሆነ፣ አስተማማኝና የተረጋጋ ዴሞክራሲያዊ የዜጎች አገር (the nation-state) ነው።

ከዚህ በላይ ዘርዘር አድርጌ በአውሮፓ የዴሞክራሲን አመጣጥ የጠቀስኩት እኛም ሶስት መቶ ዓመታት ይፍጅብን ለማለት አይደለም። ምክንያቱም በአሁኑ ዘመን እውቀቱና ተጨባጭ ምሳሌዎችም ስላሉ ሂደቱም ሆነ የሚፈጀው ዘመን እንደ አውሮፓ መሆን

---

[4] ስለ ዜግነት መብት ታሪካዊ አመጣጥ በጥልቀት ማወቅ የሚፈልግ ይህን ግሩም ጽሑፍ መመልከት ይችላል። T. H. Marshall, Class, Citizenship and Social Development, New York: Doubleday & Company, Inc. 1964.

አይችልም፣ ሊሆንም አይገባም:: ይህ እንዳይሆን ሌላው ታሪካዊ ምሳሌ ጃፓን ባለፉት መቶ ዓመታት ውስጥ እንዲሁም ታይዋን ባለፉት አምሳ ዓመታት ውስጥ የዴሞክራሲን ስርዓት መገንባት ችለዋል:: እንደዚሁም በአህጉራችን ደቡብ አፍሪካ፣ ሴኔጋል፣ ዛምቢያን የመሳሰሉት ከዚህም ባጠረ ጊዜ ዴሞክራሲን ለመገንባት የሚያደርጉት ጥረት ተስፋ የሚሰጥ ነው:: ስለዚህ እኛም በጅምር ላይ ያለውን የዴሞክራሲ ግንባታ ሂደት በቅንነት ከያዝነውና ባለመታከት ጥረት ከአደረግን የዴሞክራሲን ስርዓት በአንድ የትውልድ ዘመን ውስጥ መገንባት እንደምንችል መገመት ይቻላል::

ሌላው የአውሮፓን ታሪክና ልምድ የጠቀስኩበት ምክንያት፣ የዴሞክራሲን ግንባታ ተግባር አስመልክቶ፣ የመብቶቹ ቅደም ተከተል ሎጂክ ያለውና አንዱ በአንዱ ላይ የሚመረኮዝ መሆኑን ለማስመር ነው:: ሶስቱንም፣ ማለትም የሕግ፣ ፖለቲካ እና ማኅበራዊ መብቶች በአንድ ወቅትና በአንድ ታሪካዊ ሰነድ እራሳችን በተሳትፎና በትግል ባዘጋጀነው ሕገ መንግሥት ማግኘት ብንችል እሰዬው ነበረ:: ካልሆነ፣ ለማናቸውም የምንፈልጋቸው መብቶች የግድ በመጀመሪያ የሕግ ልዕልና ታውቆና ተከብሮ ሕጋዊ መብታችን እንዲረጋገጥ ያሳሰሰ ጥረት ማድረግ አለብን:: መጀመሪያ እያንዳንዳችን በማንኛውም ሁኔታ የሚከበር የሕግ ሰውነት ያለን የአንድ አገር ኢትዮጵያ እኩል ዜጎች መሆናችን መታወቅ ይኖርበታል::

ያለበለዚያ አንተ፣ አንቺ፣ እኔ ማንን ብለን ነው፣ እፍርድ ቤትም ሆነ ፖሊስ ጣቢያ፣ እመንግሥት መስሪያ ቤቶችም ሆነ ሌሎች አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን ቀርበን መብታችንን ማስከበር የምንችለው? የሕጋዊ ዜግነት መብቱ ካለን ግን በቀጥታ ከእየአንድአንዱ ኢትዮጵያዊ እኩል፣ የግል ችሎታችንና አቅማችን ብቻ በሚወስነው ገደብ፣ በአገሪቱ አስተዳደር ስልጣን፣ በየትኛውም ደረጃ ለመሳተፍ በሕግ መጠየቅ እንችላለን:: በሌላ አነጋገር፣ የሚያስተዳድረንን ባለስልጣን የመምረጥ፣ ችሎታው ካለን ከማንኛውም ዜጋ ጋር ለስልጣን ቦታ ለመመረጥ የመፎካከር መብት እንዲኖረን በሕግ ለመከራከር መንገዱ ክፍት ይሆናል:: የዜጎችን የስልጣን ልዕልና ማረጋገጫ መንገዱም ይኸው ብቻ ነው::

የዜጎች የስልጣን ልዕልና በአልተረጋገጠበት ሁኔታም ማኅበራዊ መብቶችን የአደባባይ የፖለቲካ ጥያቄ ማድረግ አይቻልም:: እማራጭ የፖለቲካ ዝንባሌ ያላቸው ግለሰቦችም

ይሁኑ የፖለቲካ ድርጅቶች ከሌሉና ደንብና ስርዓት ያለው የምርጫ መንገድ ከሌላ ዜጎችም ከነዚህ መካከል ይህኛው ይሻላል ብለው የሚሹትን የመምረጥ ዕድል አይኖራቸውም:: ለምሳሌ ድህነትን መቀነስ ብሔራዊ የሆነ አንገብጋቢ ጥያቄ ነው ብለው የሚያምኑ የኅብረተሰቡ አባላት አማራጭ የፖለቲካ ፓርቲዎች ባሉበት አገር ለዚህ ጉዳይ ትኩረት ይሰጣል ብለው ወደ አመኑበት ፓርቲ ሄደው ድጋፋቸውን ሰጥተው ጉዳዩም ብሔራዊ ትኩረት ተሰጥቶት መፍትሄ እንዲያገኝ ተስፋ ያለው ጥረት ማድረግ ይችላሉ:: እንዲሁም የአገሪቱ የሰው ኃይልና የገንዘብ አቅም ለጦር መሳሪያ ግዢ ከሚውል ለትምህርትና ጤና አገልግሎት ሥራ ይዋል ብሎ የአገሪቱን የማኅበራዊ መብቶች ለማስከበር ለመሞከር የፖለቲካ አማራጭ አመለካከቶችና ቡድኖች መኖር የግድ ያስፈልጋል::

ለዚህም ይመስለኛል አሁን በአገራችን በሰፋትና በአደባባይ የሚወሱትና የሚጮህላቸው ጥያቄዎች በአንድ በኩል የሕግ ልዕልና እና ለሕግ ተገዥነት ሲሆን በሌላ በኩል ደሞ የፖለቲካ አማራጭ መኖር ናቸው:: በእውነትም የሕግ ልዕልና እና አማራጭ የፖለቲካ ቡድኖችና ፕሮግራሞች በሌሉባቸው አገሮችና ሁኔታዎች ውስጥ ሰፋ ያለ በሕዝብ የሚፈለግ ለውጥ የሚመጣው በአብዛኛው በአመጽና በትጥቅ ትግል ነው::

## ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር

ከዚህ በላይ ሰፋ አድርጌ ማሳየት የፈለግኩት በጥቅሉ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ምን እንደሚመስል ነው:: ስለሆነም የተዘረዘሩት የዴሞክራሲ ገጽታዎች መልኩን (formal) በወረቀት ላይ፣ እንደ ሕገ መንግሥት ውስጥ፣ እንዳለው እንጂ የፖለቲካ ሥራ በጭብጥ ሲካሄድ እንዴት እንደሆነ በደንብ አላየንም:: ከዚህ ቀጥሎ የዴሞክራሲ ስርዓትን በተለይ ለመልካም አስተዳደር እጅግ አመቺ እንደሆነ ለማሳየት ሁለት የተዛመዱና የሚደጋገፉ የራሱ የሆኑ መዋቅራዊ ሁኔታ እንይ::

የመጀመሪያው የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥ ያለው ወይም ብዙ ጊዜ የሚገኘው ለዜጎች አመቺ የሆነ *የፖለቲካ አካባቢያዊ ዝንባሌ* (enabling political environment) ነው:: ይኸም ሶስት አይነተኛ ጉዳዮችን ያካትታል::

መልካም አስተዳደር

1. አንደኛው አመኔታ (legitmate authority) ነው:: ማንኛውም አሳማ ወይም ግብና ፖሊሲ በመንግሥትም ሆነ ወይም በተወሰኑ የኅብረተሰቡ ክፍሎች ታልሞ የሥራ ዕቅድ ከወጣለት በኋላ ስኬታማነቱ የሚረጋገጠው የሕዝቡን በተለይም የሚመለከተውን ክፍል አመኔታ ወይም በአሳማው ላይ ስምምነት ሲኖር ነው:: በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ማንኛውም ትልቅ አገር አቀፍ ዕቅድ የሚወጣው ወይ በቀጥታ በሕዝቡ ተሳትፎ ነው፤ አለበለዚያም ሕዝቡ በመረጣቸው ወኪሎች አማካይነት ነው:: ስለዚህ ከመጀመሪያው ትልሙ ሕዝብ ተወያይቶ የተስማማበት ጉዳይ ነው ወይም ወኪሎቹ የወሰኑትና በቀጥታም ወደሱ መጥተው የሚያስረዱት ስለሆነ ዕቅዱ የሕዝብ አመኔታ ያገኛል::

2. ሁለተኛው የመታረም ችሎታ ነው:: ይህ ችሎታ የሚረጋገጠው ለፖለቲካ የስልጣን ቦታ በሕግ በተወሰነ የጊዜ ገደብ በሚደረግ ምርጫ ነው:: በዴሞክራሲያዊ ስርዓት አንድ የተሳሳተና የሕዝብ ድጋፍ የሌለው ትልቅ ዕቅድ ሊቆይ የሚችለው ቢበዛ እስከሚቀጥለው የምርጫ ጊዜ ብቻ ነው::

3. ሶስተኛው ፍራቻ ነው:: በዴሞክራሲ ስርዓት ዜጎች እንዲሁም ባለስልጣኖች/አስተዳዳሪዎች ፍራቻ ቢኖራቸው ለተወሰነ በእውነትም ለሚያሰጋ አጋጣሚ ነው እንጂ ሁለገብ የሆነ ስጋትና ጥርጣሬ የለባቸውም፤ የሚተዳደሩበት ሕግና ስነ ስርዓት የተከበረና የሚያውቁት በየጊዜው የማይለዋወጥ ስለሆነ:: በአንጻሩ አምባገነን በሆነ ስርዓት ውስጥ ተራ ዜጎች ምን ጊዜም አብላጫ አቅም ላለው፣ ለባለስልጣን፣ የሚያስደንቀው ሕግ አስካባሪ ናቸው ለሚባሉት ፖሊሶችና ፍርድ ቤቶችም ጭምር ደህንነታቸውና ሰላማቸው ለአደጋ የተጋለጠ ነው:: በአምባገነን ስርዓት ውስጥ ባለስልጣኖችም በሚያደርጉት የፖሊሲ ምርጫና በሚወስዷቸው ውሳኔዎች ላይ የሚኖረው ፍራቻ የሚመነጨው ተጠያቂነታቸው ለሕዝብ ወይም ለሕግ (ብቻ) ሳይሆን ለሚሾሟቸው አለቆች ስለሆነ ነው:: ብዙውን ጊዜ በአምባገነናዊ አስተዳደር የአንድ ባለስልጣን በዚያ የስልጣን ቦታ ላይ መገኘትና መቀጠል የዋናው ጌታ ፍላጎት ነው:: በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግን ባለስልጣን ቦታውን የሚይዘው ወይ በቀጥታ በሕዝብ ተመርጦ ነው፣ ወይም የሕዝብ ተወካዮች መርጠው/ዋት ነው:: ተጠያቂነቱም ለሕዝብ፣ ለተወካዮች ምክር ቤት ወይም በሕግ ለሚታወቅ አካል ነው::

ሁለተኛው የዴሞክራሲ ስርዓት ውስጥ የሚካሄደውን የፖለቲካ ተግባር በአንድ በኩል የባለስልጣናቱን ግልጽነትና ተጠያቂነት (transparency and accountability) የሚያረጋግጥ በሁለተኛ በኩል ሲያስፈልግ የሕዝብ ድጋፍ በቀላሉ የሚገኝበት መሠረታዊ ጉዳይ *የሕዝብ የኑቃና የተደራጀ ተሳትፎ* ነው:: ይኸም ሁለት ቁም ነገሮችን ያካትታል::

1. የመጀመሪያውና ዋነኛው ለፖለቲካ የስልጣን ቦታ የሚደረገው የምርጫ ተሳትፎ ነው:: እላይ እንደተባለው ማንኛውም ዜጋ ለፖለቲካ የስልጣን ቦታ የመመረጥም የመምረጥም መብት አለው:: ምርጫ የሚካሄደውም ከጅምሩ በሕግና በስነ ስረዓት በተወሰነ መንገድ፣ እንዲሁም በጊዜና በቦታ በተካለለ ገደብ ሆኖ፣ ሂደቱም ንጹህ፣ ነፃና ርቱእዊ መሆን አለበት:: ይህ ታላቅ የፖለቲካ ተግባር በተወሰነ የጊዜ ገደብ በቀጣይ መልኩ ሲካሄድ እያንዳንዱ ዕጩ ተወዳዳሪ ሥልጣን ላይ ያለው ባለፈው ተወካይነቱ ዘመን ያደረጋቸውን ሁሉ በግልጽ የሚጠየቅበት፣ አዲስ ዕጩ ተወዳዳሪ ካሉትና ከሌሎች ተወዳዳሪዎች የሚለይበትን የሚገልጽበትና እስከ የሚቀጥለው የምርጫ ጊዜ እሠራቸዋለሁ የሚላቸውን ተግባራት በመዘርዘር ተስፋ የሚሰጥበት ሁኔታ ነው:: የነዚህን ዕጩ ወኪሎች ብቃት የሚመዝነውና የፖለቲካ ዕጣቸውን የሚወስነው የአገሩ ዜጋ ነው::

አንድ አንድ ሰዎች የምርጫን ተሳትፎ አስመልክቶ የዴሞክራሲ ስርዓት ያለውን ችግር እንደ መሠረታዊ ድክመት የሚያቀርቡ አሉ:: ይህ ችግር በሚሳተፈው ሰው ቁጥር ላይ ያተኩራል:: የሚሉትም፣ ለምሳሌ በአሜሪካ የአሁኑ ፕሬዜዳንት ለመምረጥ መብት ካለው ዜጋ ውስጥ በ29.3% ተመረጠ እንበል:: ይሄም የሚሆነው መጀመሪያ የመምረጥ መብት ካላቸው ውስጥ በነበረው ምርጫ የተሳተፉት 52.6% ብቻ ነው ብንልና ከዚህ ቁጥር ውስጥ ለሚስተር ቡሽ ድምጻቸውን የሰጡት እላይ የተባለው ከሆነ በውነትም የተመረጠው ከአጠቃላይ የመምረጥ መብት ካላቸው ዜጎች ቁጥር ሲነጻጸር በአነስተኛ ድምጽ ነው:: ሆኖም ግን አትምረጡ የሚል ትእዛዝ ወጥቶም ሳይሆን፣ የምርጫውም ሂደት በሕግ፣ ነፃና ርቱእዊ መንገድ ከተከናወነ ችግሩ የዴሞክራሲ ስርዓት መጓደል ሳይሆን የሌሎች ችግሮች ምልክት ሊሆን ይችላል:: ይኸም ችግር ብዙ ጊዜ በይፋና በአደባባይ ይተችበታል፣ መፍትሄም ይፈለግለታል:: በነገራችን ላይ በምርጫ ያለመሳተፍም መብት ነው፣ አንድ አንዴም ወይ በተመራጮቹ ወይም በያዙት

መልካም አስተዳደር

የፖሊሲና የዕቅድ አቋም ላይ ቅሬታን ለማሳየት ሊሆን ይችላል:: ይኸም ቢሆን ሌላ የሚታይ የዜጎች ተሳተፎ በግልጽ የሚንጸባርቅበት ሁኔታ አለ::

2. ይህ ሁለተኛው ዜጎች ነፃ በሆኑ ተቋማት አማካኝነት የሚያደርጉት ተሳትፎ ነው:: በዚህ በኩል ለምሳሌ በአሜሪካ የታወቁ ሶስት ተቋማት ይገኛሉ:-

    1. የኢኮኖሚው ጠንካራ ተቋማት የሠራተኛውን ማኅበር ጨምሮ፣
    2. የመገናኛ ብዙሀን፣ እንዲሁም
    3. የዕውቀት፣ ምርምርና የትምህርት ተቋማት::

የመገናኛ ብዙሀን ሚና በተለይም በምርጫ ወቅት፣ ለማንኛውም ባለስልጣን ግልጽነትና ተጠያቂነት እንደ የዜጎች አይንና ጆሮ ሆኖ ማገልገል የታወቀ ነው:: ስለሆነም የነሱን አቅም የሚያጎለብት የተለየ ሕጋዊ መብት አላቸው:: ሌሎቹ ተቋማት መንግሥታዊ ያልሆኑትን የተለያዩ የሕዝብ ማኅበራትን ጨምሮ ድጋፋቸውን በመስጠት ወይም በመከልከል በማንኛውም ለፖለቲካ ቢሮ ለሚወዳደር ዕጩ ላይ ግልጽ የሆነ የፖለቲካ ተጽእኖ አላቸው:: ይሄም ኃይል ለፖለቲካ የስልጣን ቦታ የመምረጥ ብቻ ሳይሆን የሚተለሙትን ዕቅዶችና የሚወጡትን ፖሊሲዎች ከራሳቸው ፍላጎትና ጥቅም አንጻር እንዲስተካከሉ የማድረግ ችሎታም ጭምር ነው:: ብዙ ጊዜም የነዚህ ተቋማት አንጻራዊ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ አቅም፣ የጠሩን ኃይል እንደ የሁሉም ገለልተኛ ኃይል ወደ ጎን ብናደርገው፣ በተናጥል እንኳን ከአለው የመንግሥት ኃይል ይበልጣል::

## III መልካም አስተዳደርና የኢኮኖሚ ልማት

በጥቅሉ መልካም አስተዳደር፣ ኢኮኖሚ ልማትና ድህነትን የመቅረፍ ሂደት በጽንሰ ሃሳብ ደረጃና በታሪካዊ አመጣጣቸው የሚገናኙ ብቻ ሳይሆኑ የሚዛመዱም ናቸው:: ማለትም መልካም አስተዳደርና ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ያለው አገር የኢኮኖሚ እድገትም ድህነትን የመቋቋም አቅምም ይኖረዋል:: ነገር ግን እዚህ የቀረበው

መልካም አስተዳደር → / ← የኢኮኖሚ ልማት → / ← ድህነትን መቋቋም

ከላይ በቀስቶቹ ለማሳየት የተሞከረው አንዱ የአንዱ መንስኤ ወይም ምክንያት የመሆን አስገዳጅ ሁኔታ ሳይሆን ከሞላ ጎደል ግንኙነት እንዳላቸው የታወቀ መሆኑን ነው:: ድህነትን የመቋቋም ጠባይ ከሌሎቹ ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያሳየውን መስመር የተቆራረጠ ያረግሁት ግንኙነቱ በብቃት የተሳሰረ አለመሆኑን ለመጠቆም ነው:: ለማንኛውም ድህነትን እታች በአምስተኛው ምዕራፍ ወይም ክፍል ውስጥ ለብቻው በጥልቀት ስለምናየው እዚህ በሁለቱ መካከል ባለው ግንኙነት ላይ እናተኩራለን::

## መልካም አስተዳደር

የአስተዳደር አስፈላጊነት የሚመነጨው በመሠረቱ፣ ማንኛውም ሰብጠር ያለ አላማን በተግባር ለመፈጸም፣ ቅንጅት በአስገዳጅ መልኩ ( what Weber calls "imperative coordination")[5] ስለሚያስፈልግ ነው:: ብዙ ጊዜም ይህ የተቀናጀ የድርጅታዊ አሠራር በስልጣን ሰንሰለት ተዋርድ ይዋቀራል:: ይኸም ማለት እኔና የሙያ ባልደረቦቼ ማኅበር ማቋቋም ብንፈልግ፣ የሆኑ ጓደኞች በዛ ያሉ ነጋዴዎችን አስተባብረው የንግድ ተቋም ቢመሠርቱ፣ የአንድ ቀበሌ ነዋሪዎች በቀበሌ ኣቸው የሚገኘውን ሽብርተኝነት ለማጥፋት ቢደራጁ፣ መንግሥት ድህነትን ከአገሪቱ አጠፋለሁ ብሎ ቢነሳ፣ ወዘተ፣ ሁሉም ለአላማቸው እንደአቅማቸው አመቺ የሆነ መስተዳድር መፍጠር ይኖርባቸዋል:: እነዚህም የተለያዩ አስተዳደሮች አንዱ ከአንዱ የበለጠ አሠራሩ ግልጽ፣ ለአላማው ስኬታማ፣ አባሎቹን በሚፈልጉት መጠን የሚያሳትፍ፣ የአስተዳዳሪዎቹ ስልጣን በሕግ የተወሰነ ሊሆን እንደሚችል ማናችንም መገመት እንችላለን::

እዚህ የምናወራው ስለ መንግሥት አስተዳደር ነው:: በመንግሥታት መካከል ያለውን የአስተዳደር ልዩነት ለማየት በዘመናቸው የአፄ ኃይለ ሥላሴን በኢትዮጵያ እና የኬኔዲን በአሜሪካ የነበራቸውን የአስተዳደር ገጽታ ጠቅለል ባለ መልኩ ለማየት እንሞክር::

---

[5] እጅግ ሰፋ ባለ መንገድ ጸሐፊው ይህን የቅንጅት በአስገዳጅ መልኩ አስፈላጊነትና ከዚያም ይህ ቁም ነገር ተቀባይነት ወደ አለው ስልጣን በምን በምን መንገድ እንደሚተገበር እና እንዴት እንደሚንጸባረቅ ይዘረዝራል:: Max Weber, The Theory of Social and Economic Organization. Edited with an Introduction by Talcot Parsons, New York: The Free Press, 1964, pp. 324-406.

| | <u>የቀ. ኃ. ሥ. ኢትዮጵያ</u> | <u>የጄ. ኤፍ. ኬ. አሜሪካ</u> |
|---|---|---|
| *የስልጣን ምንጭ* | ልማዳዊ መለኮታዊ | የሕዝብ ምርጫ |
| *የመንግ. ለውጥ* | ሲሞቱ ወይም በጡንቻ | በሕግ በተወሰነ ጊዜና ዘዴ |
| *የመንግ. ቁጥጥር* | የዘውድ አማካሪ፣ ቤተ ክህነት | መገናኛ ብዙሃን፣ ፍርድ ቤቶች፣ ፓርላማ |
| *የሕዝብ ተሳትፎ* | ምንም ወይም ማጨብጨብና እጅ መንሳት | ምርጫ፣ ኃይለኛና ነፃ ማኅበራዊ ተቋማት |
| *ለሕግ ተገዢነት* | እንዳስፈላጊነቱ፣ በዘፈቀደ | ነፃ የሆኑ የሕግ ተቋማት እና ሕጉ የማይለዋወጥ |
| *ኃላፊነት* | ሹመት በዝምድና፣ በታማኝነት | ሙያዊ ችሎታና ልምድ |

ከዚህ በላይ የተባለው የሁለቱን መንግሥታት ገጽታ ልዩነት በቂም ባይሆን ከሞላ ጎደል ይገልጻል:: ይሄ ማለት እላይ የተገለጹት የመንግሥታቱ ገጽታዎች አንዱጋ ያለው ሁለተኛውጋ በፍጹም የለም ለማለት ሳይሆን፣ በአመዛኙ ጠባያቸው የሚንጸባረቀው ግን እንደተባለው ነው:: በቀላሉ የሚታወቀውን ላለ ምድገም ነው እንጂ ማናችንም የትኛው መንግሥት የተሻለ መልካም አስተዳደር እንደነበረው፣ ከዚህ አገላለጽ ብቻ፣ መገመት አያቅተንም::

ፖለቲካንና ኢኮኖሚን አስመልክቶ፣ የትኛው አቅጣጫን የመቀየስና አንዱ በአንዱ ላይ ያለውን አንጻራዊ የመጫን አቅም ደግፎ የሚካሄድ የቲዮሪና የፍልስፍና ክርክር አለ:: እዚህ ክርክር ውስጥ ሳንገባ በጥቅሉ በግልጽ የሚታዩ ለኢኮኖሚ ልማት አመቺ የሆኑ የመልካም አስተዳደር ጠባዮችን እንይ:: በነገራችን ላይ የመልካም አስተዳደር ጥሩነት በእውነትና በተግባር የሚታየውም ዜጎች በየመስኩ የሚፈልጉዋቸው አስተዳደራዊ አገልግሎቶች በቀለጠፈና አመርቂ በሆነ መንገድ በፈለጉበት ጊዜና ቦታ ሲሰጣቸው

ነው። የኢኮኖሚ ልማትን አስመልክቶ ከዴሞክራሲያዊ መልካም አስተዳደር የሚሰጠውን ድጋፍ በሶስት ተዛማጅና ተደጋጋፊ መንገዶች ማየት ይቻላል።[6]

አንደኛው በፖለቲካ በተረጋጋና ሰላም በሰፈነበት ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥ የፖለቲካው አካበባዊ ዝንባሌው (political environment) የሚሰጠው ሁለገብ ድጋፍ ነው። ይህ የፖለቲካ አካበባዊ ጠባይ የሚፈልቀው ከኅብረተሰቡ የሕግ ተገዥነት እምነትና ዜጎችም በአገሩ ሕግ ፊት በእኩልነት በመታየታቸው ነው። ይህም ተፋጻሚ እንዲሆን የአገሩ ሕግ ለሁሉ ዜጋና ሁኔታ ያለ ምንም ዓይነት አድልዎ የሚያገለግል ተዘርዝረው የተጻፉ ሕግጋትና የሕግ አፈጻጸም ስነ ስርዓትን ያካተተ መሆን አለበት። በተጨማሪ ለማንኛውም ቢሮ ቅጥረያ መለኪያው የዜጋው/ዋ የሙያና የልምድ ብቃት ብቻ መሆን አለበት። እነዚህ እላይ የተገለጹት ተፈላጊ ሁኔታዎች ከተረጋገጡ ሕዝቡም በአገሩ ፖለቲካ ሂደት ውስጥ ንቁ ተሳታፊ ይሆናል።

ይኸም በመሆኑ በመጀመሪያ በመንግሥቱ ስልጣን ላይ አመኔታ ይፈጠራል። የመንግሥቱ ስልጣን፣ መሪው(ዎቹ) ያልመረጧቸው ቢሆኑም እንኳ፣ ተቀባይነት ይኖረዋል። ሁለተኛ ስርዓቱ በውስጡ የመታረም ችሎታ ስላለው፣ መሪዎቹን በጣም የማይፈልጓቸው ቢሆኑም እንኳን በሚመጣው የምርጫ ወቅት ያሉትን መሪዎች ብቻ ሳይሆን ፖሊሲዎችን ጭምር የመለወጥ ሕጋዊ ችሎታ ስላላቸው ተስፋ የመቁረጥ ዝንባሌ በብዙ ዜጎች ዘንድ አይኖርም። ሶስተኛ ለራሳቸው ህልውና፣ ለንብረታቸው ባለቤትነት፣ እምነታቸውንና እሴታቸውን ለማስተጋባት ዜጎች ፍራቻ አይኖርባቸውም። ይኸም ማለት ከልማት አንጻር እያንዳንዱ ዜጋ በግልም ሆነ በማኅበር ተደራጅቶ አቅሙን፣ ንብረቱንና ያጠራቀመውን ገንዘብ በማቀናጀት ሕይወቱን ለማሻሻልም ሆነ ለመበልጸግ ያለ ብዙ ተጽእኖ አቅሙ በፈቀደ መጠን መጣር ይችላል። ይህ የእያንዳንዱ ዜጋ ጥረት ሲጠራቀም የአገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት ሞተር መሆን እንደሚችል ጥርጥር የለውም።

---

[6] እኔ በአጭሩ እዚህ ላማቀርበው ትንተና ከሚከተለው መጽሐፍ ብዙ ሃሳቦች ወስጃለሁ። Lucian W. Pye, Aspects of Political Development, Boston: Little, Brown and Company,1966.

## መልካም አስተዳደር

ሁለተኛ በዴሞክራሲ ስርዓት ውስጥ የሚገኙ ማናቸውም የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የዜጎቹን ፍላጎት ምንጊዜም እግምት ውስጥ የማግባት ጠባይ ነው:: በእርግጥ ይህ ሊሆን የሚችለው አቅሙ ካለ ነው:: በዴሞክራሲ ስርዓት ውስጥ የአስተዳደሩ አቅም መዳበር መጠን በሶስት መንገዶች ይታያል:: አንደኛ በሚያስተዳድረው አገራዊ ጉዳዮች ስፋትና ጥልቀት ነው:: ለምሳሌ ያህል ከአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት የኬኔዲው የአሜሪካ መንግሥት አስተዳደር በበለጠ አገሩ ውስጥ ያለውን የማይነካውና የማይገባበት የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ጉዳዮች የሉም:: ሁለተኛ የአስተዳደሩ የቢሮ ስርዓቶች የመንግሥቱን ፖሊሲና ዕቅዶች በተግባር በመተርጎም ስኬታማ (effective) እና ቀልጣፋ (efficient) መሆናቸው ነው:: ይህም ማለት የመልካም አስተዳደሩ ቢሮዎች በሙያተኛ ሠራተኛ የታነጹ አሠራራቸው ግልጽ (transparent) እና የሥራቸውም ውጤት የሚለካና ለቁጥጥር የሚያመች (accountability) መሆኑ ነው:: ሶስተኛ በመረጃና በሰሌት የተገነባ፣ ዘዴውንና ግቡን በአገናዘበ መልኩ የፖሊሲና ዕቅድ የማዘጋጀት ችሎታ ነው::

በተለይ ኢኮኖሚውን በተመለከት መንግሥት አጠቃላይ አገራዊ ኢኮኖሚው ውስጥ (macro economic environment) የተዛነፉ አሥራሮችን፣ የገንዘብም ሆነ የገበያ ወይም ግሽበትን፣ በማረምና በማስተካከል ለሁሉም የኢኮኖሚ ተግባር ተሳታፊዎች አመቺ ሁኔታን ለመፍጠረ ጥረት ያደርጋል:: እያንዳንዱ ኢኮኖሚ ነክ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችም፣ ግብር ሰብሳቢዎቹ፣ የጉምሩክ ድርጅቶቹ፣ የተለያዩ የገንዘብ ተቋማት ባንኮቹን ጨምሮ፣ የተለያዩ የመገናኛና የመጓጓዣ መሰረተ ልማት ድርጅቶች፣ የተለያዩ የኢኮኖሚ መረጃ ያላቸው ድርጅቶች፣ ወዘተ፣ ፈጣንና የተቀላጠፈ አገልግሎት ለአምራቹና ለነጋዴው መስጠት በሕግ ይጠበቅባቸዋል:: የነዚህ የቢሮ ስርዓቶች ሥራቸው ግልጽ እንዲሆንና ኃላፊነታቸው ተጠያቂነት እንዲኖረው ሁሌም፣ ዜጎችም፣ የመገናኛ ብዙሃኑም እንዲሁም ተፎካካሪዎቻቸው አፍጥጠው ነው የሚጠባበቋቸው:: በአደጉት የአንደኛ አለም ኅብረተሰቦች ዘንድ መንግሥት የሕዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋም ሆኖ መታየት በጣም እያደገ ነው የመጣው::[7] እነዚህ ተቋማት ብዙ ጊዜም ከግሉ ኢኮኖሚ ክፍል ተወዳዳሪዎች አሏቸው፣ አገልግሎት አቅርቦታቸው በሚታይ መንገድ ከደከመም ወደግል ይዞታ የሚለወጡበት መንገድ ይፈለጋል::

---

[7] ለምሳሌ፣ David Osborne and Ted Gaebler, Reinventing Government: How the Entrepreneurial Spirit is Transforming the Public Sector. New York: Plume, 1993 ይመልከቱ::,

ሶስተኛው የመልካም አስተዳደር ገጽታ የሚታየው ባለው የተግባር ክፍፍል (differntiation) ነው:: ይህም ሂደት በአንድ በኩል የሥራ የተለየ ሙያዊ ትኩረት (specialization) ሲያጠናክርና ሲያስፋፋ፣ በአንጻሩ እነዚህ የተለያዩ ተግባራትና ሙያዎች በተቀናጀ (integration) መልኩ ሳይጋጩ መሥራት አለባቸው:: ጥሩ ምሳሌ ከዚህ በላይ ለማቅረብ እንደተሞከረው በዴሞክራሲ ስርዓት ውስጥ የፖለቲካው አስተዳደር አካል ከኢኮኖሚው አካል ጋር የተከፋፈለ ሆኖ፣ እንዲህ እንዲሆንም ይፈለጋል፣ ተደጋጋፊና በአጠቃላይ ኅብረተሰቡ ሲታይ የአንድ አካል (integrated) ሁለት ክፍሎች መሆናቸውን እንረዳለን:: በሌላ ዋነኛ የኅብረተሰብ አካል ውስጥ፣ የሕግ አውጪው ክፍል የሕግ ስርዓቱን አፈጻጸም ሳይጫነው፣ እንዲሁም የአስተዳደሩ ባለሥልጣናት የሕግ አተረጓጎም ሥራ ውስጥ ጣልቃ ሳይገቡ ግን በመተባበርና እርስበርስ በመቆጣጠርና በመተራረም ሲሠሩ ይታያሉ:: የመገናኛ ብዙሃን፣ የትምህርትና ምርምር የተለያዩ ተቋማት፣ ወዘተ፣ በዚህ መልኩ ኅብረተሰቡ ውስጥ የሚታወቅና የሚከበር ቦታ ይዘው በመተጋገዝ እና በመተራረም አብረው ይዳብራሉ::

እነዚህ የተለያዩ ተቋማት በአንድ በኩል ለእራሳቸው እድገት በቂ ነፃነት ያላቸው ስለሆነ በሂደት በየጊዜው መሻሻልና የሙያዊ ፈጠራም ያሳያሉ:: በመሠረቱም ይህ የዴሞክራሲ ስርዓት ሁነኛ የተቋማት አቅም መፍጠሪያ ማዳበሪያ ዘዴ ነው:: ይኸም አቅም ለኢኮኖሚው ዋና ዋና ተዋንያን፣ ማለትም ለአምራቹና ለነጋዴው፣ በቅርበት የሚገኝ ነው:: ይህ ብቻም አይደለም፣ አምራቹና ነጋዴው ያለውን የገንዘብ አብላጫ አቅም በመጠቀምም ሆነ ተሚጋቾቹን (lobbyist) በተገቢው ቦታ በማሰማራት የሚወጡትን ሕጎች፣ የምርምርና የጥናት ግኝቶች፣ ዕቅዶችና ፖሊሲዎች ለእርሱ ተስማሚ እንዲሆኑ ማድረግ ይችላል፣ እግባብም አለው::

እስካሁን ከላይ የቀረበው ከሞላ ጎደል የምዕራባውያንን ታሪካዊ ተሞክሮ በመውሰድና በሎጂክም የአንድ አገር ፖለቲካ እና ኢኮኖሚ መተሳሰራቸው ብቻ ሳይሆን መደጋገፋቸው ለላቀ ኅብረተሰብ እድገት አስፈላጊ ነው ብሎ በመገመት ነው:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን አንድ አንድ ጥናቶች በተለይም ተቋማት እና ሙስና የኢኮኖሚ ልማት ሂደት ላይ ያላቸውን ቀጥተኛ ተጽእኖ ማሳየት ጀምረዋል:: ከዚህ የበለጠም ሶስት

የአለም ባንክ የምርምር ሰዎች የ150 አገሮችን ሁኔታ አጥንተው የተሻለ አስተዳደር በቀጥታ የተሻለ የልማት ውጤት እንደሚያስገኝ መረጃ አቅርበዋል። ያደረጉት 300 የሚሆኑ የመልካም አስተዳደር አመልካቾችን ጨፍልቀው ከስድስት የመልካም አስተዳደር ጽንሰ ሃሳቦች ጋር አያያዟቸው። ጽንሰ ሃሳቦቹ "ድምጽና ተጠያቂነት፣ የፖለቲካ አለመረጋጋትና የጡን ቻ ሽብር፣ የአስተዳደር ስኬታማነት፣ የቁጥጥር ሸክም፣ ለሕግ ተገዥነት እና ሙስና" ናቸው። ከዚያ በኋላ የረቀቀ የአሃዛዊ ጥናት ስሌት በመጠቀም በእነርሱ አባባል መልካም አስተዳደር በእርግጥ የተሻለ የልማት ውጤት ያመጣል። በዚህ ጥናት ስልት የአንድ (standard deviation) ቁጥር የአንዱ የመልካም አስተዳደር አመልካች ላይ ብቻ እንኳን መጨመር ከሁለት ተኩል እስከ አራት እጥፍ ጊዜ የሰዉን ገቢ መጠን (per capita income) ይጨምረዋል ወይም ይቀንሰዋል፣ እንዲሁም ከ15 እስከ 25 በመቶ የማንበብና የመጻፍ ችሎታን ይጨምረዋል።[8] የነዚህ ጥናት ግኝቶች በመሠረቱ እላይ በጥቅሉ ለተባለው ክርክር ተጨማሪ ተጨባጭ መረጃ በመሆን ክርክሩን ያጠናክሩታል።

## የኢኮኖሚ ልማት

የኢኮኖሚ ልማትም በአብዛኛው እስከ አሁን የመልካም አስተዳደር ምሳሌ አድርገን የወሰድናቸው ምዕራባውያን አገሮችና ጃፓን ውስጥ ነው የሚታየው። መልማት ብቻም አይደለም በተናጥል አካባቢያቸውን፣ በአሜሪካ መሪነት በወል የአለምንም የካፒታል ክምችት፣ እሉ የሚባሉትን የማምረቻ ኃይሎችንና ገበያውንም ይቆጣጠሩታል። እርግጥ በየዓመቱ እየተገናኙ ይደራደራሉ ይመካከራሉ፣ ነገር ግን አለምን እንዲህ አድርገን እንቆጣጠረው ብለው አይዶሉትም አያሲሩም። ሆኖም የአለም የኢኮኖሚና የፖለቲካ ሂደትም በዘፈቀደም አይደለም። ከላይ እንደተባለው በተዋቀረና በተቀናጀ መንገድ ከመወያየትና ከመደራደር ባሻገር የካፒታሊስት እድገትና ስርዓቱ በካፒታሊስት

[8] Daniel Kaufmann, Aart Kraay and Pablo Zoido-Lobaton, "Good Governance Matters", Policy Research Working Paper 2196, The World Bank, October 1999, pp.61 esp. p.6.

የማምረትና ገበያ ሎጂክ ላይ የተመሠረተ ነው። ለማንኛውም የካፒታሊስት የኢኮኖሚ ልማት መንገድ የሚከተሉት ዓይነተኛ ገጽታዎች አሉት፡-[9]

1. ነፃ የሆኑ የአምራችና የንጋዴ ድርጅቶች (enterprises) ቀሳቀሳዊ የማምረቻ ኃይሎችን እንደ ግል መገልገያ ንብረት ማከማቸትና መጠቀም መቻል። እነዚህ የማምረቻ ኃይሎች የሚያጠቃልሉት መሬትን፣ ገንዘብን፣ ማንኛውንም ዓይነት መሳሪያዎችን፣ ወዘተ፣ ነው።

2. ነፃና ክፍት የሆነ ገበያ ሊኖር ይገባል። ይህም ማለት ገበያው ከማንኛውም ከንግድ ስሌት ውጭ ነፃ ቁክክርንም ሆነ የገብያን ዋጋ ከሚወስን ክባህላዊ ወገም ሆነ ከመደብ በጠቅላላው ከማናቸውም ገደብና ጣላቃ ገብነት ነፃ መሆን አለበት። ገበሬ መሬቱን ሸጦ የመደብ ሕይወቱን መለወጥ የማይችል ከሆነ፣ በኅብረተሰቡ ውስጥ ያሉ የተለያዩ ክፍሎች ማንኛውንም ዓይነት ሸቀጥ በሞኖፖል ከያዙት፣ ወዘተ፣ የሸቀጥ ንግድ ነፃነትም ሆነ የሠራተኛ ነፃ ገበያም አይኖርም።

3. በቀላሉና በግልጽ እግምት ውስጥ የሚገባ ሕግ መኖር አለበት። ይህም ማለት ሕጉ ከዛሬ ነገ የማይለዋወጥ ሆኖ የካፒታሊስት ስርዕት ነጋዴም ሆነ አምራች በአስተማማኝ ሁኔታ የሕጉን ስነ ስርዓትና አፈጻጸም እስሌት ውስጥ ማግባት መቻል አለበት።

4. እንዲሁም ነፃ ተንቀሳቃሽ የሆነ የሠራተኛ ኃይል መኖር አለበት። ይኸም የሚሆነው ሰዉ በፍላጎት ብቻ ሳይሆን ለመኖር የኢኮኖሚው ሁኔታ አስገድዶትና ኑሮውን ለማሻሻል በሚያደርገው ጥረት ላይ የተመሠረተ ነው።

እነዚህ ሁሉ የካፒታሊስት ስርዓት ጠባዮች ከዚህ ስርዓት በፊት በነበሩ ማናቸውም ዓይነት የኅብረተሰብ ቅንብሮች ውስጥ በተሟላ ሁኔታ ኖረው አያውቁም። ወደ

[9] ከዚህ በታች የሚዘረዘሩት የካፒታሊስት ስርዓት ገጽታዎች የተቀናበሩት ከሚቀጥሉት መጽሐፍቶች ነው። Max Weber, General Economic History. New York: Collier Books, 1961, esp. ch. 22 "The Meaning and Presuppositions of Modern Capitalism", and Neil J. Smelser, The Sociology of Economic Life. Englewood Cliffs: Prentice-Hall Inc., esp. ch. 5 "Sociological Aspects of Economic Development."

መጀመሪያ ላይ እንዳየናቸው የሕግ፣ የፖለቲካና የማኅበራዊ መብቶች እነዚህም የኢኮኖሚ ልማት አመቺ ሁኔታዎች የተገኙት በተመሳሳይ ትግል ነው፡፡ እነዚህ የካፒታሊስት ስርዓት የኢኮኖሚ አራት ገጽታዎች በሙሉ የሚያገለግሉት የካፒታል ክምችት እንቅፋት እንዳይገጥመው እና የመስፋፋት ዝንባሌውም በምንም ሁኔታ እንዳይገደብ ነው፡፡ የካፒታሊስት ስርዓት ግንባታ ማንኛውንም ዓይነት የገበያ ነፃነትና ክፍትነትንም ሆነ የሠራተኛን የመዘዋወርና ተቀጥሮ የመሥራት መብትን የሚገድቡ፣ የካፒታል ንብረት ባለቤትነት ዋስትና የማይሰጡ ፊዩዳላዊ ወጎችም ሆኑ ሕጎች መደምሰስ የመጀመሪያ ተግበሩ ነበር፡፡

ይህ የካፒታል ክምችት ለበለጠ ክምችት ሎጂክና የመስፋፋት ዝንባሌ ገና ከጅምሩ ለማምረቻ ተፈላጊ ግብአቶችን ለማግኘትና ለሸቀጡም ሰፋ ያለ ገበያ ፍለጋ ከራሱ ድንበር ክልል በጊዜ ነው መውጣት የጀመረው፡፡ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ሎጂክና እላይ የተጠቀሱትም አይነተኛ ገጽታዎች በአገሩ ውስጥ እንደሚያገለግሉ ሁሉ አለምንም አገናኝቶና አገናዝቦ ማየት ከተቻለ ከሞላ ጎደል በተመሳሳይ ሁኔታ አለም አቀፍ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ስርዓትንም ያገለግላሉ፡፡ የሚገድባቸው በወቅቱ ያላቸውና ሊጠቀሙበት የሚችሉት የመገናኛ ቴክኒክና ድርጅታዊ ዘዴ ነው፡፡ እነዚህ ቴክኖሎጂዎች በተራቀቁና የድርጅቱም አቅም በዳበረ መጠን መስፋፋቱና መቆጣጠሩም ያን ያህል ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡ ይኸው ከቀጥተኛ የቅኝ ግዛት መስፋፋት በኢምፔሪያሊዝም አግድሞ ድንበር የለሽ ቅንጅት (globalization) ደረጃ ደርሰነናል፡፡

ከዚህ ስርዓት ግንባታ ሂደት ጋር ተያይዘውና በኢኮኖሚ ልማቱ ተደግፈው የሚያድጉ ሌሎች አራት ማኅበራዊና የቴክኖሎጂ ለውጦች አሉ፡፡

1. አንደኛ ቴክኖሎጂን በተመለከተ ለውጡ በተለምዶ ከሚሠራባቸው ቀላል ዘዴዎች ሳይንሳዊ ዕውቀትን መጠቀም ነው፡፡ ሳይንሳዊ ዕውቀት ላይ ተመሥርቶ በመገናኛ ዘዴዎች፣ በመጓጓገርያ መሠረተ ልማቶች እንዲሁም ድርጅታዊ አቅም በመፍጠር ችሎታ የተደረገው ምጥቀት እያንዳንዱ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ተቋም ከማጠናከሩ ባሻገር አለም አቀፍ ካፒታሊስት ስርዓትንም ለመገንባት ዓይተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

2. ሁለተኛ ግብርናን በተመለከተ ለራስ ኑሮ ብቃት ላይ ብቻ ከተመሠረተው (subsistence agriculture) እርሻ ወደ ገብያ እሚቀርቡ ሰብሎች (commercial agriculture) ማምረት ላይ መሸጋገር ነው። ይህ ማለት የእርሻ ማምረት ተግባር ገቢያ ላይ በሚቀርቡ ሰብሎች ላይ ማተኮር ብቻ ሳይሆን ገበሬውም ሌሎች ፍላጎቶቹን ለማሟላት በገቢያ መጠቀምና ለገበያ ግብርና ሥራና ለኢንዱስትሪዎችም ተጨማሪ ሠራተኛ መገኘት ጥሩ ዘዴ ነው። የገበያ እርሻ ማደግ ደግሞ ምግብ በማምረት የላቀ ዘዴ ስለሆነ በከተማ ለሚጠራቀመው ሰው በቂ ምግብ እንዲኖር አረጋገጠ።

3. ኢንዱስትሪን አስመልክቶ ለውጡ በእንስሳትና በሰው ጉልበት ብቻ ከመጠቀም ወደ በሞተር በሚንቀሳቀሱ መሣሪያዎች ተጠቅሞ ምርትን አሳድጎ ወደ ገበያ የማቅረብ ዝንባሌ መሸጋገር ነው። የኢንዱስትሪ ማደግ ለሸቀጣ ሸቀጦች መስፋፋትና በዓይነታቸው መብዛትም ሆነ ለጥራታቸው የላቀ የማምረት ዘዴ ነው። ለካፒታሊስት ስርዓት ኢኮኖሚ የመስፋፋት ሎጂክ ዓይነተኛ አጋዥ እርምጃም ነው።

4. በመጨረሻም ዓይነተኛ ለውጡ የሰዉ አኗኗርና በአካባቢ አሰፋፈር ፈሊጥ ነው። የቴክኖሎጂው እድገት የፈጠረው የላቀ የመገናኛና የመጓጓዣ አገልግሎት እንዲሁም ቀልጣፋና ስኬታማ ድርጅታዊ አቅም፣ በእርሻ በኩል የተገኘው ምርታማነት፣ በኢንዱስትሪ የተስፋፋው ተፈላጊ ሸቀጣ ሸቀጥ ከገጠር የመንደር አኗኗር ሰፋ ወደ አለ የከተማ ኑሮ (urbanization) መሸጋገርን አመጣ። ይኸም በጠ ባብ ቦታ ሰፋ ያለ ገበያን በመፍጠርና የሸማቹን ቁጥር በመጨመር ለካፒታሊስት ኢኮኖሚ እድገት የራሱን አስተዋጽኦ አድርጓል።

እነዚህ ለውጦች በተለይም በተናጥል ከካፒታሊስት ስርዓት በፊት በነበሩ ኅብረተሰቦች ውስጥ የሉም ወይም አልነበሩም ሳይሆን በካፒታሊስት ስርዓት ውስጥ ግን እነዚህ አስፈላጊ ሁኔታዎች በስፋት ይገኛሉ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜም እያደጉ ሲሄዱ እናያለን።

በዚህ የካፒታሊስት ስርዓት የሚረጋገጠው ምርት በስፋት፣ በዓይነትና በጥራት ተፈብርኮ የሰዉንም ፍላጎት የሚያረካ ሽቀጣ ሽቀጥ በገበያ መገኘቱ ነው። በተጨማሪም ከዓመት ዓመት፣ ኢኮኖሚውን የሚያቃውስ አዲስ ነገር ካልተፈጠረ፣ ኢኮኖሚው ያድጋል የሰዉም አማካይ ገቢ ይጨምራል። ሆኖም ግን የካፒታሊስት ስርዓትን በሚከተሉ አገሮች ሁሉ የሚኖረው ሕዝብ የኑሮ ደረጃ በተለይም የሕይወቱና የኑሮው መልካምነት (quality of life) በተመሳሳይ ሁኔታ ያምራል ማለት አይደለም። የገቢ ምንጭ በርቱአዊነት እንዲሰራጭ፣ የሰዉ የኑሮ ደረጃና የሕይወት አቋም እንዲሻሻል ኢኮኖሚያዊ ያልሆኑ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ እርምጃዎች መወሰድ ይኖርባቸዋል።

## በመልካም አስተዳደርና በኢኮኖሚ ልማት መካከል ያለው ግንኙነት

በዕውቀት ደረጃ የነዚህን ማኅበራዊ ክስተቶች ትስስር ምን ያህል እንደሆነ በመረጃ የተደገፈ ጥናታዊ ግኝት በጣም ትንሽ ነው። ትምህርቱም ሆነ የምርምር ሥራው የሚካሄደው በተከፋፈለ፣ ማለትም ስነ መንግሥት ወይም የፖለቲካ ጥናት፣ ስነ ኅብረተሰብ፣ ስነ ኢኮኖሚ፣ ስነ ልቡና፣ በሚሉ የዕውቀት ክልል ተቀናጅቶ ነው። ሆኖም፣ እላይ ከገጽ 8 እስከ 10 ከተባለው በተጨማሪ፣ በቂ ባይሆኑም እንኳን በተለይ ከስነ ኅብረተሰብ የተለያዩ ሥራዎች እንዲሁም በቅረቡ ከሚደረገው የአዲሱ የስነ ኢኮኖሚ ተቋማትን የሚያገናዝብ ሙከራ (the new institutional economics) በቀረቡ ሃሳቦች ላይ በመመርኮዝ ጠቅለል ባለ መልኩ ግልጽ የሆኑት ግንኙነቶቻቸው ከዚህ ቀጥሎ ይቀርባሉ።[10]

በፖለቲካ ወይም በመልካም አስተዳደርና በኢኮኖሚ ልማት መካከል ያሉት ግንኙነቶች በብዛት ግልጽ ናቸው። ለምሳሌ ያህል የሚሠራ ግልጽ የሆነ የሕግ ስርዓት መኖሩ

[10] The most useful concepts from the NIE approach are "transaction costs" and "collective action", and from sociology the ideas of an "interchange system" with a structure of dominance between subsystems of a social structure as for example between the polity and economy. For NIE approach see "Institutions, Resources and Development in Ethiopia" in Proceedings of the Ninth Annual Conference on the Ethiopian Economy, Eds. Alemu Mekonnen and Dejene Aredo, Septmber 2000. For the sociological concepts see Talcot Parsons, Sociological Theory and Modern Society, New York: The Free Press, 1967.

ለሁለቱም ጠቀሜታ ያለው ነው፣ እንዲሁም በሥራው ቀልጣፋና ስኬታማ የሆነ የቢሮ ስርዓት። ስለዚህ በነዚህ ተግባራት ሁለቱ ተደጋጋፊ ናቸው ማለት ይቻላል። ግብርን በተመለከተ የሁለቱ ተቋማት የጥቅም አስተያየት የተለያየ ከመሆኑም በተጨማሪ ሊጋጭ የሚችልበትም ሁኔታ አለ። የፖለቲካው መሪዎች ብዙውን ጊዜ የመንግሥትን አቅም የሚያጎለብቱት በግብር ከሚሰበስቡት ገንዘብ በመሆኑ የግብር ከፍ ማለት ሲጠቅማቸው ካፒታሊስቱን ግን ይጎዳዋል። በጥቅሉ በረጅም የጊዜ ክልል ውስጥ ሲታይ የአንድ አገር የኢኮኖሚ ይዘት ለአስተዳደሩ ገጽታና አቅም ላይ የተወሰነ ተጽእኖ ይኖረዋል። ማለትም ለምሳሌ በግብርና ላይ የተገነባ ስርዓት ውስጥ የተሟላ ፋሽስታዊም ሆነ ዴሞክራሲያዊ የአስተዳደር መዋቅር መፍጠር ይቸግራል። እንዲሁም የቡርዡዋው ክፍል በአደገበት የካፒታሊስት ስርዓት ውስጥ ሁለገብ የሆነ አምባገነናዊ አስተዳደር ብዙ ሊቆይ አይችልም። በአጭር የጊዜ ክልል ውስጥ የአስተዳደሩ ስልጣን በኢኮኖሚው ላይ በቀጥታ ተጽእኖ ማድረግ ይችላል። የአጠቃላዩን የኢኮኖሚ ተግባር የሚጻናወቱ ወይም የሚደግፉ ፖሊሲዎችን አውጥቶ ተግባራዊ በማድረግ የኢኮኖሚውን ሁኔታ ሊደግፍም ሊያበላሽም ይችላል።

የፖለቲካንና የኢኮኖሚን ግንኙነት በተቀነባበረ መንገድ ለማየት መጀመሪያ የሰነ ኅብረተሰብ አባባልን እንመልከት። የፖለቲካ አጠቃላይ ተግባር በስልጣንና ኃይል ላይ የተመሠረተ ሲሆን፣ የኢኮኖሚ ደግሞ በገንዘብና በንብረት ላይ ነው። ብዙ ጊዜም አንዱ የሌለውን ሌላው ስለሚፈልገው በሁለቱ መካከል መለዋወጥ ማለትም የኢኮኖሚ ባለጸጋው ገንዘብና ንብረት ሰጥቶ ከፖለቲካ መሪዎች የባለስልጣንን ድጋፍ ወይም የሚፈልገውን የፖሊስ ውሳኔ መጠየቅ መኖሩ የታወቀ ነው። ልውውጡም አይኑን ያወጣ ሙስና ሳይኖርበት በብዙ ቦታዎች የተለመደ አሠራር ሆኖ፣ የግንኙነቱን ወሰን የሚያካልል ሕግም ሲወጣለት ይታያል። በዚህም መንገድ ካፒታሊስቱ አመቺ የሆኑ የፖሊሲና የመንግሥት ትላልቅ ኢኮኖሚ ነክ ዕቅዶችን እንዲነደፉ ይጥራል፣ በአንጻሩ በተለይ በፖለቲካ ምርጫ ወቅት ተወዳዳሪዎች ለምርጫ ማካሄጃ የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ ከባለሀብቶች ማግኘት ይፈልጋሉ።

እንዲሁም በኢኮኖሚ ሥራ ውስጥ የተቋማትን ተጽእኖ የሚያገናዝበው አዲሱ የጥናት ዘዴ የሚለው ማንኛውም የኢኮኖሚ ተግባር የመደራደርና የአፈጻጸም ተጨማሪ ዋጋ

(transaction cost) አለበት:: ከብዙ በጥቂቱ፣ አስተዳደርን አስመልክቶ ውሎችን መረጃ ላይ በተመሠረተና ግልጽ በሆነ ስምምነት መጨረስ መቻል፣ የንብረት የግልም ሆነ የወል ባለቤትነት ቀጥተኛ ዋስትና ኖሮት መጠቀም፣ ማንኛውም ተፈላጊ መረጃ በቀላሉና በቅርቡ መገኘት፣ ወዘተ በተቋማት ሲደገፍ የመደራደርና የአፈጻጸም ተጨማሪ ወጋን ይቀንሰዋል:: እንዲሁም በቀጥታ ከፖለቲካ መሪዎችና ፓርቲዎች ጋር የሚዛመደው የነሱን የፖለቲካ አመለካከትና ርዕዮተ አለም እንደ ዓይነተኛ በኢኮኖሚ ስሌት ውስጥ የሚገባ ነገር አርጎ ይወስዳል:: የኛን አገር በተመለከተ ድህነት በተለይ የመንፈስ ድህነት እንደ ቅኝት ማጣት፣ ፍራቻ፣ ከኃላፊነት መሸሽ ዓይነቶች (ገጽ 24 ይመልከቱ) በኢኮኖሚ ተግባር ውስጥ ያላቸው አሉታዊ ተጽእኖ ከባድ ዋጋ መስላት ያለበት ጉዳይ ይመስለኛል::

ይህ በኢኮኖሚ ተግባር የመደራደርና የአፈጻፀም ዋጋ፣ በተለይም ሳይንሱ ረቆና በመረጃ ዳብሮ በሚቀርብበት ወቅት፣ በአለም አቀፍ ደረጃ ለሚካሄደው የንግድ ልውውጥና ፉክክር ልዩ የሆነና የሚለካ መልእክት ይኖረዋል:: በጥቅሉ አለም አቀፍ የካፒታሊስት ስርዓት ውስጥ በሶስተኛና በአንደኛ አለም አገሮች መካከል በስርዓቱ ሎጂክ የሚኖረው ማናቸውም ልውውጥ በምንም አኳኋን እኩል መሆን እንደማይችል ነው::[11] ይህን መልእክት በሚቀጥለው ምዕራፍ የአገራችንን ሁኔታ ስናጤን አንድ ምሳሌ ማየት እንችላለን::

## IV. የታዳጊ አገሮች መልካም አስተዳደርና የኢኮኖሚ ልማት ሁኔታ

በዚህ ምዕራፍ ከላይ በቀረቡት ሁለት ክፍሎች ስለ መልካም አስተዳደርና ኢኮኖሚ ልማት የተባለውን እንደ መንደርደሪያ በመውሰድ በታዳጊ አገሮች ላይ እናተኩራለን:: ለአቀራረቡ እንዲያመቸኝ በኢኮኖሚ ልማት እጀምራለሁ::[12] ከዚያ በፊት ግን ስለጥገኛ

---

[11] See Arrighi Emmanuel, Unequal Exchange. New York: Monthly Review Press, 1972 and Samir Amin, Unequal Development: An Essay on the Social Formation of Peripheral Capitalism. New York: Monthly Review Press, 1976.

[12] ምክኒያቱም በተለይ ለኛና እኛን ለሚመስሉ የሶስተኛ አለም አገሮች በአሁን ወቅት የተወሰኑ የኢኮኖሚ አላማዎች በተግባር ከአልዋሉ እንደ አገርና እንደ ልዑላዊ መንግሥት ለመኖራችን ማረጋገጫ የለም:: ረሃብንና ችጋር-ድህነትን ከአልተቋቋምን፣

*የልማት መንገድ*[13] አንዳንድ ጽንሰ ሃሳቦች ማወቁ በመቀጠል ስለ ኢኮኖሚ ልማት ለሚባለው ጉዳይ ግልጽ ግንዛቤ ይረዳል:: ጥገኛ ልማት ከስነ ኢኮኖሚ ሳይንስ አንድ ጠበብ ያለ ክፍል ነው:: የዚህን ክፍል የጥናት ግኝት በጣም እንዳልበደልኩት ተስፋ በማድረግ ጠቅለል አድርጌ ዋና ዋና ሃሳቦቹን በነጥብ መልክ ከዚህ ቀጥዬ አቀርባለሁ::

1. የጥገኛ ልማት ጥናት ከኢምፔሪያሊዝም ጥናታዊ ግኝት የቀጠለ ነው::

2. መነሻ ሃሳቡ ማንኛውም ዓይነት የኢኮኖሚ ልማት ወይም የካፒታል ክምችት በውጭ ኃይሎች ተጽእኖ ካለበት ጥገኛ ይባላል:: ለጥገኝነት መንስዔውም የአለም አቀፍ የካፒታሊስት ስርዓት ሎጂክና እኩል ያልሆነ የልውውጥ/የገበያ ግንኙነት ነው:: ይህ ግንኙነት አንድ አንዴ የመካከልና ዳር ያሉ አገሮች (አለም አቀፍ የካፒታሊስት ስርዓትን በማገናዘብ) ግንኙነት ተብሎ ይጠራል (center and periphery)::

3. ሙሉ ጥገኛ ኢኮኖሚ መደበኛ ወይም የመጀመሪያ ደረጃ ምርቶች፣ ማለትም ከመሬቱና ከአካባቢው የተገኙትን ከሞላ ጎደል እንዳሉ፣ ለውጭ ገበያ የሚያቀርብና ከውጭ ደሞ የተፈበረኩ ምርቶችን የሚቀበል ነው::

4. ጥገኛ ልማት ማድረግ ይቻላል:: ይህም የሚፈጸመው ጥገኛ ኢኮኖሚ ያለው አገር የኢንዱስትሪ ምርቶች በፋብሪካ አምርቶ ለአለም አቀፍ ገበያ ማቅረብ ሲቻለው ነው:: ብዙ ጊዜ ግን ይህ የዳር አገር ልማት በካፒታሊስት ስርዓት ኃያላን ማእከሎች የተወሰነ ነው::

---

በከተማዎቻችን ለተጨናነቀው በተለይ ወጣት ሥራ አጥ ሠርቶ የሚኖርበት ሁኔታ ከአልፈጠርን ወደፊት በዚሁ ምክንያት ሊመጣ የሚችለው ማኅበራዊ ቀውስና ሽብር ኅብረተሰቡን ይሰብረዋል ብዬ እገምታለሁ::

[13] ቀጥሎ የማቀርበው ክርክር ወይም መንደርደሪያ ሃሳቦች የተወሰዱት ከላይ በቁጥር 10 ከተጠቀሱት መጽሐፍት በተጨማሪ በተለይም ከሚቀጥለው መጽሐፍ ነው:: Peter Evans, Dependent Development: The Alliance of Multinational, State and Local Capital in Brazil, New Jersey: Princeton University Press, 1979.

መልካም አስተዳደር

5. የጥገኛ ልማት ካፒታል ክምችት ዋና ተዋንያን ብሔራዊ ከበርቴው፣ የውጭ ኢኮኖሚ ተቋማት እና መንግሥት ናቸው:: በነዚህም መካከል ያለው ግንኙነት ቅራኔ የሞላበት ነው::

እነዚህን ጽንሰ ሃሳቦች በመጠቀም የማንኛውንም ሶስተኛ አለም አገር የኢኮኖሚ ልማት ሂደት ማጥናትና መተንተን ይቻላል::

## ኢኮኖሚ ልማት

አሁን በአለንበት ዘመን ለኢኮኖሚ ልማት በካፒታሊስት የማምረት ዘዴ፣ ምርቱን በነፃ ገበያ የመለዋወጥና የሕዝቡም ፍላጎት በገበያ ላይ በተመሠረተ አቅርቦትና ፍጆት መገልገል የተሻለ አማራጭ የለም:: ሌላው የካፒታሊስትን ስርዓት መከተል አስገዳጅ የሚያደርገው በአሁኑ ወቅት ያለው ድንበር የለሽ አለም አቀፍ አወቃቀርም በዚሁ ስርዓት ላይ የተመሠረተ መሆኑ ነው:: ሌላ የተሻለ እንደ ሶሻሊዝም ያለ አማራጭ በጽንሰ ሃሳብ ደረጃ መተለም ቢቻልም ይህ እንደ አማራጭ የሚሆነው አሁን ይኸንኑ የካፒታሊስት ስርዓት ለሚመሩት በስልጣኔና በልማት ለዳበሩት አገሮች ብቻ ነው:: ምን አልባት እንደ የተለየ ምሳሌ ታላቂቱ ቻይናን መጥቀስ ቢፈለግም ለጊዜው የአብዛኛው ታዳጊ አገሮች ሁኔታ ቻይናንም በምንም መልኩ አይመስልም:: ቻይና በጣም ትልቅ አገር ናት:: የመልክዓ ምድሩ ስፋትና የሰዉ ቁጥር ብዛት አንድ ዓይነተኛ ኃይል ነው:: በዚህ ላይ በተፈጥሮ ለኢኮኖሚ ልማት ተፈላጊ የሆኑት ግብአቶች ከሞላ ጎደል ሁሉም አሏት:: ይሄ ሁሉ ተደምሮ አሁን ከአላት የእድገት ደረጃ ጋር ሲቀመር ቻይና ካለም የካፒታሊስት ስረዓት አድራጊ ፈጣሪዎች ጋር የመደራደርና በገለልተኛነት በራሷ መንገድ የመሄድ ችሎታ ካላቸው በጣም ጥቂት አገሮች አንዷ ነች::

አገራችንም የምትከተለው ይህንኑ የካፒታሊስት ጎዳና ነው: ኢኮኖሚውም በውነት ጥገኛ ነው:: ይኸን እንደ ጭብጥ የአገራችን ሁኔታ ለመቀበል ሁለት ዓይነት መረጃዎች ብቻ ይበቁናል:: አንደኛ የአለብን የብድር እዳ መብዛት ነው:: ዶ/ር በፍቃዱና ዶ/ር ብርሃኑ እንደሚሉት ከአራት ዓመት በፊት የነበረብን እዳ 649 ሚሊዮን ዶላር ነበር፣ ይህም እየጨመረ ይሄዳል እንጂ የሚቀንስበት ምንም ዓይነት ምልክት የለም:: እንደሚሉትም የብድሩ መብዛት የመጀመሪያው ዋና ተጠቂ የኢኮኖሚ ልማት ነው:: ምክንያቱም

የብድሩን ወለድ እንኳን የመክፈል ግዴታው ወደፊት ኢንቬስት እናደርጋለን ብለን ያሰብነውን ወደ ውጭ አበዳሪዎች ጋር መላክ አለበት። በተጨማሪም የመንግሥቱን የፖሊሲ ምርጫ ነፃነት ይገድበዋል። በዚህም ምክንያት መንግሥት የአልፈለጋቸውን የፕሮግራም ቅድመ ሁኔታዎች ለመቀበል ተገዷል። አብዛኛው አበዳሪዎቹም የካፒታሊስት አገሮች መንግሥታትና የነሱ አለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማትና ባንኮች ናቸው።

ጥገኛ ኢኮኖሚ እንላለን የሚያመለክተው ሁለተኛ መረጃ ወደ ውጭ የምንልካቸው ሸቀጦች በሙሉ የእርሻ ጥሬ ምርት ናቸው በአመዛኙ ያው ቡናና ቆዳ። በአንጻሩ ከውጭ የምናስመጣቸው በአብዛኛው የተፈበረኩ እቃዎች ሲሆኑ እነዚህም ብዙ ጊዜ እላቂ ናቸው። በብዛትም የምንሸጠውና የምንሸምተው የላቀ ግንኙነት ያለን ከአውሮፖውያን ጋር ነው፣ በአንጻሩ ከአፍሪካ ጋር ያለን ግንኙነት በጣም ትንሽ ነው። ከዚሁ ጋር የሚያያዘው ሌላው የኢንዱስትሪ እድገት ኢኮኖሚው ምንም አያሳይም፣ የፋብሪካና የኢንዱስትሪ ምርት ውጤት ድርሻ ለአጠቃላይ የአገሩ ምርት ዝቅተኛ መሆኑ ብቻ ሳይሆን እየቀነሰ ነው ወይም በአንድ ቦታ ቆሟል።[14]

እላይ እንደተባለውም በታዳጊ አገሮች ተንቀናቂ የኢኮኖሚ ዘርፍ ውስጥ ሚና ያላቸውና የካፒታል ክምችት ስራ ውስጥ የሚንቀሳቀሱት መንግሥት፣ የውጭ ተቋማትና በከተማዎች ውስጥ የሚገኙ ባለሃብቶች ናቸው። እኛ አገር መንግሥት ከበፊተኛው እዝ ኢኮኖሚ ከወረሳቸው የንግድና የምርት ተቋማት በተጨማሪ ስልጣኑን በያዙት የኢህአዴግ ፖለቲካ ፓርቲዎችም ስም የያዛቸው ትላልቅ የምርትና የንግድ ተቋማት አሉት። እነዚህን የጥገኛ ልማት ጸሐፊዎች የሚጠሯቸው የመንግሥት ከበርቴ ብለው ነው። እነዚህ ላይ የቢሮውን ስርዓት የሚመሩትን ከፍተኛ ደሞዝተኛ ባለስልጣናትን ብንጨምርበት በውነትም በአገራችን አቅሙ ሰፋ ያለ የኢኮኖሚ መደብ ነው።

[14] Annual Report on the Ethiopian Economy, Eds. Befekadu Degfe and Berhanu Nega. Addis Ababa, United Printers, 1999-2000, እላይ ለቀረበው የብድር ጉዳይ መረጃ ገጽ 275-79 እና ለንግድ ልውውጥ 259-262፣ 240-243 ይመልከቱ።

በአገራችን በፖሊሲ ደረጃ ብሔራዊ የግል ባለሃብቱ ይበረታታል ቢባልም እስካሁን ያለው ሁኔታ ግን የመንግሥት ከበርቴውና የግል ባለሃብቱ በጎሪጥ ነው የሚተያዩት። የብሔራዊ ከበርቴው አባላት እንዲሁም የተበጣጠሱ ናቸው በተጨማሪም ግን መንግሥት የብሔራዊ ከበርቴውን አምራች ባለሀብትና ኪራይ ሰብሳቢ በሚል ስያሜ ከፋፍሎ የባሰ ግራ አጋብቷቸዋል። እንደ አንዱ ጸሐፊ አባባል አለም አቀፍ ከበርቴውማ እንደ እንጀራ ልጅ ነው የሚያያቸው። የሚያደላው በግብርና ላይ ተመስርተው ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡትን ከበርቴዎችና ሸቀጭ አቀባባይ ከበርቴውን ነው።[15] ቅራኔው እንዳለ ሆኖ ግን ግንኙነት በመካከላቸው ለመኖሩ አሁን በሙስና ተከሰው እስር ቤት ያሉት ሰዎች ዓይነት ይመሰክራሉ። ለማንኛውም ግን አሁን ባለው የኢኮኖሚ ሁኔታና ለመጪውም እግምት ውስጥ ለሚገባ ዘመን ብሔራዊ ከበርቴው የራሱ ራዕይ ኖሮት በፖለቲካ ኃይል የሚገፋው ጉዳይ ትንሽ ነው።

የአለም አቀፍ ካፒታል ኢኮኖሚ ወኪሎች እምብዛም እንደ ሁለቱ በይፋ አይታዩም። ምን አልባትም የካፒታል ጥቅማቸውን የሚያራምዱት በጥቂት የራሳቸው ወይም በአገሬው ሰው ተወካይ ይሆን ይሆናል፣ በሚስጥርም ይሁን በይፋ ግን ከመንግሥት ባለስልጣናት ጋር መገናኘታቸው የማይቀር ነው።

የሶስቱንም መደብ አባላት ግንኙነት የሚያመለክቱ፣ በቀጥታ ኢኮኖሚ ጉዳይ ባይመስሉም፣ ሌሎች የአኗኗር ዘይቤዎች አሉ። ምን አልባትም ብዙ ጊዜ የሚገናኙት ተራ ሕዝብ ሊሄድ የማይችልበት ቦታዎች ነው፣ ለስፖርትም ሆነ ለጫወታ የሚዝናኑበትም ቦታ ለየት ያለ ይሆናል። ስልኩም ሆነ ፋክሱ ወይም በኮምፒዩተር መገናኘቱም በራሳቸው መካከል የተለለ ሆኖ ከዚያም ናይሮቢ ከሞምባሳ፣ ዳካር ከሴንትልዊ ወይም አዲስ አበባ ከሀረር ጋር ከሚገናኙበት በተሻለና በተቀላጠፈ መንገድ ከለንደን፣ ፓሪስና ኒውዮርክ ጋር ይገናኛሉ። የመንግሥትና የግል ባለሃብቶቹና ዘመዶቻቸው የሚታከሙት፣ ልጆቻቸውም የከፍተኛ ትምህርት የሚከታተሉት፣ በዚሁም ምክንያት ገንዘባቸውን የሚያስቀምጡት የካፒታሊስት ስርዓት መሪዎች አገሮች ውስጥ ነው።

---

[15] Peter Evans, op. cit. p. 39.

ዋናው ነገር አሁን ባለው አለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሁኔታ በብዙ ታዳጊ አገሮች ኢኮኖሚ በተለይም አንደኛ ወደኋላ ለቀሩቱ የካፒታል ክምችት ተግባራቸው እዚህ ግባ የማይባል ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ማንኛውም ዓይነት ኢንቬስትመንት ወደኛ ብቻ ሳይሆን በአጠቃለይ ወደ ታዳጊ አገሮች የሚመጣው ቀንሷል። ከዚያ በላይ ግን ታዳጊ አገሮች የሚገባው ቴክኖሎጂም ሆነ ካፒታል በአለቀለት መልኩ ነው። የአንዱ ዘርፍ ኢኮኖሚ ከሌላው ጋር ያለው ትስስር ትንሽ በመሆኑ ከውጭ የሚመጣው ካፒታል፣ አዲስ ቴክኖሎጂም ሆነ ፋብሪካ፣ ለሌላው የሚተራረፍ ጥቅም (windfall profits) እያስገኘም፣ ለሌሎች ዘርፎችም (multiplier effect) የሚሰጠውም ድጋፍ የለም። በእንጻሩ የኑሮ ሁኔታቸው የተቀረውን ኅብረተሰብ በተለይም ድሃውን ያገልላል፣ እንዲሁም የሠራተኛ ደሞዝ ማነስ በእንጻራዊ ጥቅም ስም የሠራተኛው የኑሮ መሻሻል አለመኖሩ አንዱ የጥገኛ ልማት ስልት ነው።

በተለይ በኛ አገር፣ በዚህ ላይ ተደርቦ ያለው ሁኔታ ደሞ የኅብረተሰቡ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ገጽታ ነው። ወደ 85 በመቶው ገጠሬና በግብርና የሚኖር ነው፣ እዚያም ውስጥ በዘላንነትና በከብት ርቢ የሚኖረው ሰው ቁጥር ትንሽ አይደለም። የአገሪቱ መኅበራዊም ሆነ የመገናኛ መሠረተ ልማት ኋላ ቀር ነው፤ በመንገዶች መዳረስና በቴሌኮሙኒኬሽን ስርጭት፣ የሕዝቡ የትምህርትና ጤና ሁኔታ፣ ወዘተ፣ ከአፍሪካ አገሮችም እንኳን ያነሰ ነው። እነ ዶ/ር በፍቃዱ በመጽሐፋቸው መግቢያ እንደሚሉት የአገሪቷ የቅርብ ጊዜ ዕቅድ መሆን ያለበት የድህነት ቅነሳ ተግባር ነው–ኢኮኖሚ ልማት ወደፊት ይደረስበታል።

በአጠባቃይ የአኮኖሚያችን ድቀት ዋናው ምክንያት የአለም አቀፍ የንግድ ስርዓት ለኛ በፍጹም የማያመች መሆኑ ነው። በጥቅሉ ገበያውን ከመቆጣጠራቸው በሻገር አንጻራዊ የማምረትና የመነገድ እውቀት ብልጫቸው ከፍተኛ ነው። አሁን አሁን ይኸንን ብልጫ በአሀዝ ለክቶ መናገር የሚቻልበት ዘዴ አለ። ይኸውም ተቋማትን የሚያገናዝብ አዲሱ ስነ ኢኮኖሚ (the new institutional economics) ነው። በሶስተኛ አለም በሚገኙት ከበርቴዎች እና በውጭው ከበርቴ መካከል ያለውን የመደራደርና የአፈጻጸም ዋጋ (transaction cost) ልዩነት ቢነጻጸር ትልቅ ልዩነት እንደሚኖር ጥርጥር የለውም። የኛዎቹን የመደራደርና የመፈጸም አቅም የሚገድቡ ሁኔታዎች እጅግ ብዙ ናቸው አላይ

ከተጠቀሱት ድክመቶች በተጨማሪ የገበያችን ጥበትና አማራጭ ገበያ ማጣት፣ ሙያተኛ የሆነ የሰው ኃይል በብቃት ያለመኖር፣ መረጃና የቴክኖሎጂ እውቀት ማነስ፣ የመሠረተ ልማት አውታሮቻችን ድክመት፣ የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ ስለሆነም ያሉት ማኅበራዊ ግጭቶችና ሰላም ማጣት፣ ድህነትና ችጋሩ፣ በነዚህ ሰበብ የሚፈጠር ፍራቻና ጥርጣሬው::

የቀድሞው የቬኔስዌላ ፕሬዚዳንት ፔሬዝ፣ የቀድሞው የጃማይካ ጠቅላይ ሚኒስትር ማንሊይ፣ የፓኪስታኑ ኖብል ሎሬት ሚስተር ሳላም እንዲሁም ብዙ የታወቁና ለአገራቸው ተቆርቋሪ የሆኑ ስመ ጥር ሰዎች የተሳተፉበት "የደቡብ ኮሚሽን" ለዚህ የሶስተኛ አለም አገሮች አስከፊ የኢኮኖሚ ችግር እንደ ዋነኛ መፍትሄ ያቀረቡት የእርስበርስ ትብብርና (South-South Cooperation) ክልላው የኢኮኖሚ ትስስርን ነው:: በሊቀመንበሩ የቀድሞው የታንዛንያ ፕሬዚዳንት ኒሬሬ አባባል "የደቡብ ክፍል ልማት ኃላፊነት የሚውለው በደቡብና የደቡብ ሕዝቦች ጫንቃ ላይ ነው::[16]

## መልካም አስተዳደር

መልካም አስተዳደር ሲባል ቶሎ ብሎ አሳባችን ውስጥ በጥቅሉ የሚመጣው የዴሞክራሲ ጥያቄ ነው:: የዴሞክራሲ ጥያቄ እንደ የዜግነት መብቶች፣ ነፃና ርቱእዊ ምርጫ፣ የውክልና ጽንሰ ሃሳብ፣ የመሳሰሉት ለዴሞክራሲ አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎች የመገኘታቸው ጥያቄ ደሞ እጅግ ሰፋ ያለ ከመሆኑ ባሻገር የእኛን በመሰሉ አገሮች ውስጥ የሃሳቦቹ በጥራት መታወቅና የመንግሥታቱ ጠባይ ላይም በተግባር መገለጽ ጉዳይ አሻሚ ነው:: ሆኖም ያሉት መንግሥታትም ሆኑ ዕርዳታ ሰጪ አለም አቀፍ ተቋማት በሥራ ላይ የሚያውሉት የልማትም ሆነ ድህነትን ለመቅረፍ የሚያደርጉት ጥረት ሰዉ ስለ ዴሞክራሲ ሲከራከር የሚያደርገውን ትግልና ውጣ ውረድ የሚፈጅበትንም ጊዜ እምብዛም ከስሌት ውስጥ አያገቡትም:: የዴሞክራሲ ጥያቄም መልስ እስኪያገኝ አይጠብቁም:: በአንጻሩ ዴሞክራሲያዊ ጠባይ የሌላቸው አገሮች ነገር ግን የኢኮኖሚ እድገት

---

[16] " The Report of the South Commission, The Challenge to the South. Oxford: Oxford University Press, 1990. ጥቅሱ የተወሰደው ከገጽ vii ነው::

ያሳዩና ድህነትን የመቋቋም አቅም የፈጠሩ ነበሩም እሉም–ለምሳሌ ደቡብ ኮሪያ፣ የፒኖሼ ቺሊ፣ ታላቂቱ ቻይና፣ ወዘተ::

በተጨማሪም የቡርዤዋ ዴሞክራሲን፣ ላይ እንዳየነው፣ ከከበርቴ የካፒታል ክምችት ጋር ማያያዝ አይቻልም::[17] ስለዚህ ይህ ጥናት፣ የዴሞክራሲው ጥያቄ እንዳለ ሆኖ፣ የተዘጋጀው በአገራችን ያለውን መንግሥት አሁን ካለው ገጽታ ጋር እንዳለ በመቀበል ነው:: በጥብቅ ለሚተሳሰሩት ለኢኮኖሚ ልማት በጥቅሉና በተለይ ድህነትን የመቅረፍ ሥራ ምን ዓይነት ገጽታ ያለው መልካም አስተዳደር ያስፈልጋል የሚለውን ጥያቄ በተናጥል ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት ምን መደረግ እንዳለበት ጠቅለል ባለ መልኩ መጠቆም ይሞከራል:: በተለይ የዚህ አዲሱ የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ (PRSP) ዝግጅት ተግባራት ብዙ የዴሞክራሲን መገንባት ጅምር የሚያመቻቹ ዝንባሌ አላቸው:: እነዚህን ያለው መንግሥት እንዴት እንደሚጠቀምባቸው ወደፊት የምናየው ጉዳይ ነው::

የኛን አገር በተመለከተ አንድ ነጥብ ማንሳት እወዳለሁ:: የኢትዮጵያ የመንግሥት ስርዓት ለብዙ ዘመን በአፄያዊ ንጉሠ ነገሥት አስተዳደር ተዋቅሮ ነበር:: ይህንን ስርዓት የየካቲት 1966 አብዮት ቀይሮታል:: ሲቀይረውም የመንግሥቱን ስርዓት ብቻ ሳይሆን መለኮታዊ የሆነውን የስልጣን ምንጩን አመለካከትና እምነት ጭምር ነው:: ከዚያን ጊዜ ጅምሮ ግን ምንም እንኳን በተከታታይ የመጡት ሁለት መንግሥታት የስልጣን ምንጩ ሕዝቡ ነው ብለው ደጋግመው ከመናገር አልፈው በሕገ መንግሥታቸውም ውስጥ ቢያስገቡትም በተግባር ተፈጻሚ ሆኖ ባለመታየቱ የተስማማንበትና የተቀበልነው የምናምነው የፖለቲካ ስርዓት ገና አልታነጸም:: በኔ እምነት ከማንኛው ብሔራዊ ተግባር በቅድሚያ የፖለቲካ ስርዓቱን ማስተካከል ለሌሎቹ ችግሮቻችን የመፍትሄ ፈር ቀያሽ ነው እላለሁ:: ምክንያቱም ዜጎች የሚቀበሉት የፖለቲካ ስርዓት መኖር ለአገር መረጋጋትና ሰላም ቅድመ ሁኔታዎች ነው::

---

[17] As Evans says "the association of bourgeois democracy and capitalist accumulation no longer holds" Peter Evans. op. cit. p. 47.

መልካም አስተዳደር በስነ ኅብረተሰብ ጥናት ውስጥ በተለያየ አቅጣጫና የተለያየ ትኩረት ተሰጥቶት ይተነተናል። እነዚህ ጥናቶች ውስጥ በብዛት የሚጠቀሱ ሶስት ዓይነተኛና መሠረታዊ ሃሳቦች ይገኛሉ። እነዚህንም እንደገና አጠር ባለ መልኩ መድገም ይጠቅም ይሆናል፡-[18]

1. በመጀመሪያ ሁሉም የሚያቀርቡት ሃሳብ *እኩልነት* ነው። ዜጎች ቢያንስ በአገሩ ሕግ ፊት በእኩልነት የሚታዩ መሆን አለባቸው። ይህም ተፋጻሚ እንዲሆን የአገሩ ሕግ ለሁሉ ዜጋና ሁኔታ ያለ ምንም ዓይነት አድልዎ የሚያገለግል ተዘርዝሮ የተጻፈ ሕግጋትና የሕግ አፈጻጸም ስነ ስርዓትን ያካተተ መሆን አለበት። ሁለተኛ ለማንኛውም የፖለቲካ ቢሮ ቅጥሪያ መለኪያው የዜጋው/ዋ የሙያና የልምድ ብቃት ብቻ መሆን አለበት። ሶስተኛ እላይ ያሉት ተፈላጊ ሁኔታዎች ከተረጋገጡ ሕዝቡም በአገሩ ፖለቲካ ሂደት ውስጥ ንቁ ተሳታፊ ይሆናል።

2. ሌላው ዋነኛ የመልካም አስተዳደር ጠባይ *አቅም* ነው። የዚህም አቅም መዳበር በሶስት መንገዶች ይታያል። አንደኛ በሚያስተዳድረው አገራዊ ጉዳዮች ስፋትና ጥልቀት ነው። ሁለተኛ የአስተዳደሩ የቢሮ ስረዓቶች የመንግሥቱን ፖሊሲና ዕቅዶች በተግባር በመተርጎም ስኬታማ (effective) እና ቀልጣፋ (efficient) መሆናቸው ነው። ይህም ማለት የመልካም አስተዳደሩ ቢሮዎች በሙያተኛ ሠራተኛ የታነጹ አሠራራቸው ግልጽ (transparent) እና የሥራቸውም ውጤት የሚለካና ለቁጥጥር የሚያመች (accountability) መሆኑ ነው። ሶስተኛ በመረጃና በስሌት የተገነባ፣ ዘዴውንና ግቡን በአገናዘበ መልኩ የፖሊሲና የዕቅድ የማዘጋጀት ችሎታ ነው።

3. ሶስተኛው የመልካም አስተዳደር ገጽታ የሚታየው ባለው የተግባር ክፍፍል (differntiation) ነው። ይህም ሂደት በአንድ በኩል የሥራ የተለየ ሙያዊ ትኩረት (specialization) ሲያጠናክርና ሲያስፋፋ፣ በአንጻሩ እነዚህ የተለያዩ ተግባራትና ሙያዎች በተቀናጀ (integration) መልኩ ሳይጋጩ መሥራት አለባቸው።

---

[18] ለጥናቶቹ ዓይነት ዝርዝርና እዚህ እኔ በአጭሩ ለማቀርበውም ትንተና የሚከተለውን መጽሐፍ ይመልከቱ። Lucian W. Pye, op. cit.

በዚህ መልኩ የተዋቀረ መስተዳድር ከዚህ መልካም ገጽታው የሚፈልቁ፣ ለቀጣይነቱ ማረጋገጫ የሚሆኑ ሌሎች ተዛማጅ ውጤቶች አሉ::

1. አንደኛው *የስልጣን አመኔታ ማግኘት* ነው:: አንድ መንግሥት ከሚነዛው ከማንኛውም ዓይነት ፕሮፓጋንዳ የበለጠ ከላይ የተጠቀሱት የመልካም አስተዳደር ጠባዮች ካሉት የሕዝብ አመኔታ ይኖረዋል::

2. ሁለተኛ ሕዝቡ በአገሩ ጉዳዮች ላይ ንቁ *ተሳትፎ* ይኖረዋል:: መንግሥትም በጠየቀው ጊዜ ድጋፉን ያለማመንታት ይሰጣል::

3. ከነዚህ የፖለቲካ አዎንታዊ ግኝቶች በተጨማሪም ሶስተኛ በአገሩ *የፖለቲካ መረጋጋት* እና

4. አራተኛ *ሰላም* ይሰፍናል::

አሁን ያለንበትን ወቅታዊ አስቸጋሪ ሁኔታ በመገንዘብ፣ ከላይ በተባለው ላይ በመመርኮዝና አስተዳደራችን ላይ በማተኮር፤ በእኔ ግምት ለመልካም አስተዳደርም ሆነ ለወደፊት ማኀበራዊና የኢኮኖሚ ልማት ስራ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል የምላቸውን ግልጽና ቀጥተኛ የሆኑ ሁለት ተመክሮዎች አቀርባለሁ:: በመጀመሪያ የማቀርበው የሚመለከተው በአስተዳደር፤ በተለይም አገልግሎት ሰጪ በሆኑት መሥሪያ ቤቶች የተሰለፉትን ዜጎች ነው:: ከእሴብት የቢሮ ግዳጅ በተጨማሪ ተግባራቸውን በአግባቡ መፈጸም የዜግነት ግዳጅ ጭምርም ነው:: ሁለተኛው መንግሥታችንን ይመለከታል::

አንደኛ አሁን በወቅቱ የሚሠራው ማናቸውም ሥራ ውጤት እንዲኖረው መጣር የዜግነት ግዳጅ ነው:: ይህ እንዲሆን በእውነት በእኩልነት የአንድ አገር ዜጎች መሆናችንን ምን ጊዜም አለመዘንጋት:: ስለሆነም ነጋዴው ስለንግድ አምራቹም ስለምርት፤ ተማሪውና አስተማሪው ስለትምህርቱ እስጣጥና አካባቢው አመቺነት፣ ወዘተ፣ ጉዳይ ያገባዋል(ታል):: ማናቸውም ፍትህ ፈላጊ ፍርድ ቤት፣ የስልክ፤ ኤሌትሪክ፣ ውሃ፣

መልካም አስተዳደር

ወዘተ አገልግሎት ፈላጊ ወደ አዲስ አበባ መስተዳድር የሚመለከተው መሥሪያ ቤት የሚሄደው ዜጋ ሁሉ ተፈላጊውን አገልግሎት ማግኘት መብቱ(ቷ) ነው::

ስለዚህ ተጠቀሚውና ባለስልጣኑ ይፋ በወጣና በተዋቀረ መልኩ መወያየት መመካከር አላባቸው፣ አግልግሎት ፈላጊው ዜጋ ሁሉ በአግባቡ አገልግሎት ማግኘት አለበት:: እንዲሁም ማንኛውም ባለስልጣን፡ በተለይ የበላይ ባለስልጣናት፣ ጠቅላይ ሚንስትሩን ጨምሮ፣ ስልጣኑንም ሥራውንም ከባልደረቦቹ ጋር ተከፋፍሎ መሥራት አለበት፣ ይህም የቢሮ ስርዓት የሚወስነው ግዳጅ መሆን አለበት:: የዚህ ስሜት በመጀመሪያ መመሥረት የሚገባው ሁላችንም እኩል ዜጎች ነን ብለን በምንስማማው ማኅበራዊ ውል ላይ ነው:: ሁለተኛ ባለስልጣኑ ወይም አገልግሎት ሰጪው የተቀመጠበት ቢሮ የተገነባው፣ የቢሮው እቃና መሣሪያ የተገዛው፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋወረ መንገድ፣ በአገር በሕዝብ ሃብት ነው:: ይኸም ብቻ አይደለም እነዚህም ዜጎች የሚከፈላቸው ደሞዝ ከሕዝብ በተሰበሰበ ግብር ነው:: በኔ ግምት ይህ ሃቅ በዜጎች መንፈስ የሰረጸ ጊዜ እላይ አቅም ብለን ያሰመርንበት የመልካም አስተዳደር ተፈላጊ ገጽታ በአብላጫው ተገኘ ማለት ነው:: በእውነት በሥራ መስክ ያለው የዜጎች ግንኙነት እጅግ ብዙው የዚህ ዓይነት ግንኙነቶች ናቸው::

ሁለተኛ መንግሥት ጠበብ ያለና ተጨባጭ ዜጎች የሚሳተፉበት ውጤቱን በቀላሉ ሊገነዘቡት የሚቻል ግብ ያስፈልገዋል:: አሁን ባለንበት አገራዊ አስፈሪ ሁኔታ ድህነትን መቋቋም ዓይነተኛ፣ ግብረ ገባዊና ፀጋ ያለው አላማ ነው:: በግልጽ የሚታየውና በአሃዝ ተጠንቶ በአንጻራዊ መልኩ ሲቀርብማ የሚያስፈራው በአገራችን ካሉ ብዙ ዓይነት ችግሮች ሁሉ የሚበልጠው የድህነት ሁኔታ ነው:: መንግሥታችን ድህነትን መቀነስ ተግባር ላይ የሚረባረበው የአለም አቀፍ የካፒታሊስት የገንዘብ ተቋማት ስላሉት ብቻ መሆን የለበትም:: ለመንግሥታችን ገፋፊ መንስኤ የሆኑ በቂ ሁለት ምክንያቶች አሉ::

1. አንደኛ ድህነት በከፋ መንገዱ ያለና ከወዲሁ ከአልተቋቋምነው ለሰላማችንና ለፖለቲካ መረጋጋታችን ጠንቅ ስለሚሆን፣

2. ሁለተኛ ድህነትን የመቋቋም ጥያቄ አገራዊ ማኀበራዊ ስምምነት ያለበት ብቸኛ ችግር በመሆኑ ነው:: በእውነት ድህነትን የመቋቋም ጥያቄ ማናቸውም ባለፈው ሩብ ምእተ ዓመት የገነባናቸው የርእዮተ ዓለምም

ሆን የጎሳ ወይም የመደብ ልዩነቶቻችን ሳይበክሉትና ሳይመርዙት የምንወያይበት አርእስት ነው።

ይህም እንደገና እንደ ግዳጅ ሆኖ መወሰድ ያለበት ዜጎች ሁሉ እኩል ናቸው ብለን በምንገባው ማኅበራዊ ስምምነት መሠረት ነው። ደሞ፣ ለአንድ ግለ ሰብ ህቅ እንደሆነ ሁሉ፣ ለመንግሥትም አንድ የተወሰነ አላማ ተልሞ፣ እቅምንና ማናቸውንም ያለቱን ግብአቶች አቀናጅቶ የተሳካ አመርቂ ውጤት እንደ ማየት ያለ የሚያኮራና በራስ መተማመንን የሚፈጥር ተግባር ብዙም አላውቅ።

ከዚህ በተጨማሪ የመልካም አስተዳደር ገጽታና ከኢኮኖሚ ልማትም ጋር ያለው ግንኙነት በተጠቆመበት ቦታ የተጠቀሱ መንግሥታዊ አስተዳደርን መልካም የሚያደርጉ ብዙ ዘዴዎች አሉ። በተለይም አንድ የአለም ባንክ ጠበብቶች ጥናት የፖለቲካ መረጋጋትና ሰላም፣ ተጠያቂነትና ስኬታማነት፣ የቁጥጥር ትኩረት መንዛዛት እና ሙስና በቀጥታ የልማት ውጤት ላይ ተጽእኖ እንዳላቸው በመረጃ አሳይቷል። እነዚህም ሁሉ ሊሞከሩ ይገባል። ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ተመክሮዎች ከሞላ ጎደል ሥራ ላይ ከዋሉና አመርቂ ውጤት ካላቸው፣ በተደጋጋሚነት ሕዝብ በመንግሥት ተግባር እመኔታ ይኖረዋል በተጠየቀም ጊዜ ተሳትፎውንና ድጋፉን ይሰጣል። እንዲህም ሲሆን ነው የፖለቲካ መረጋጋትና ማኅበራዊ ሰላም የሚኖረው።

## V- ድህነት በኢትዮጵያ

የካፒታሊስት ስርዓት መስፋፋት ጅምር ላይ የገጠመው ትልቅ ችግር ድህነትን መቋቋም ነበር። የድህነት ችግሮቹም በመሠረቱ የስርዓቱ ሎጂክና ሂደት ሊቋቋማቸው የማይችል በሂደቱም፣ ማለትም ስርዓቱ በሚገነባበት ወቅት በተጨማሪ ዘዴ ባልታ ገብቶ ካልገደቡት፣ ከራሱ ጠባይ የሚፈጠሩ ናቸው። እነዚህ የድህነት ችግሮች ከወዲሁ ተዘጋጅተን በዕቅድ ካልተቋቋምናቸው እኛንም ወደፊት የሚገጥሙን ናቸው። ዋነኛና ዓይነተኛ የድህነት ችግሮች ሶስት መልክ አላቸው። አንደኛው ማንኛውም ስርዓት ውስጥ በሚኖረው ክፍተት ምክንያትና በግለ ሰቡም ድክመት የተነሳ ብዙ ዱር የሚያድሩ ድሃ ሰዎች ይኖራሉ። የተቀሩት ሁለቱ የከበርቴ ስርዓት ሎጂክ የሚፈጥራቸው ናቸው።

አንደኛው ለራስ ኑሮ ብቃት ላይ ብቻ ከተመሠረተው እርሻ (subsistence agriculture) ወደ ገበያ የሚቀርቡ ሰብሎች (commercial agriculture) ማምረት ዘዴ ሲሸጋገሩ የሚፈጠር ነው። የንግድ እርሻዎች ዝቅተኛ ከሆነው እራስን ለማስተዳደር ከሚከናወነው እርሻ በሁለት መንገድ የተለዩ ናቸው። ርመጀመሪያ መሬት በስፋት ያስፈልጋቸዋል። ሁለተኛ በእንስሳትና በሰው ጉልበት ብቻ ከመጠቀም አልፈው በሞተር በሚንቀሳቀሱ መሣሪያዎች በመጠቀም በጥቂት ገበያ ላይ ሊውሉ በሚችሉ ሰብሎች ላይ ያተኩራሉ። ለሥራቸውም አስፈላጊ የሆኑትን ሳይንሳዊ እውቀቱ የሚፈለስፈውን ማናቸውንም የላቀ ዘዴ በመጠቀም ብዙ የሰው ኃይል ሳያስፈልግ ምርቱ ግን በጠራና ለገበያም ረከስ ባለ ዋጋ ማቅረብ ይችላሉ። እነዚህ ጥቂት የነጋዴ ገበሬዎች በአካባቢያቸው በብዛት ከሚገኘው ዝቅተኛ ገበሬ ጋር የሚኖራቸው ሁለገብ የሆነ አንጻራዊ የበለጠ አቅም በቀላሉ የሚታይ ነው።

ይኸን አንጻራዊ የአቅም ብልጫ በመጠቀም ለሚፈልጉት ሰፊ መሬት ወይ ለግጦሽና ለተለያዩ ጉዳዮች ተራው ገበሬ ይጠቀምበት የነበረውን መሬት በማጠር፣ ያለበለዚያም ግብር ለመክፈልም ሆነ ሌሎች ፍላጎቶቹ፣ ለምሳሌ ልብስና እራሱ የማያመርታቸውን ሸቀጦች፣ ወዘተ ለመግዛት ገንዘብ ለማግኘት ገበያ ላይ የሚያመጣቸውን ምርቶች በማራከስ ተራውን ገበሬ ምርጫ ያሳጡታል። ተራ ገበሬውም ኑሮው እጅግ ሲመረውም መሬቱን ለነሱ ሸጦም ሆነ ለቆ ለነዚሁ ነጋዴ ገበሬዎች ተቀጣሪ ሠራተኛ ይሆናል

ያለበለዚያም በተስፋ ወደ ከተሞች በብዛት ይፈልሳል። ይህ እንግዲህ አንዱ ድህነት የሚፈጠርበት መንገድ ነው።

ሁለተኛው ከገጠር ኑሮ ወደ ከተማ ኑሮ መሸጋገር ምክንያትና በከተሞችም የሚኖረው የሕዝብ ብዛት የሚፈጥረው የድህነት ችግር ነው። በዚህ ሽግግር በመጀመሪያ ድህነት የሚያጠቃው ላይ የተጠቀሰውን ዓይነት ያለምንም ዝግጅትና የከተማ ኑሮ ተሞክሮ ከገጠር በሰፋት የሚፈልሰውን ሰው ነው። ሁለተኛ የካፒታሊስት ስርዓት በጠባዩ ትርፍ ማግኘትና ይኸንንም አከማችቶ ለበለጠ ትርፍ ማዋል ሎጂክ ላይ የተመሠረተ ነው። ትርፉም ከሌሎች ካፒታሊስት ግለ ሰቦች ወይም ድርጅቶች ጋር በሚደረግ የናጠጠ ፉክክር በመሆኑ ካፒታሊስቱ እምብዛም ለድሃ ዜጋ የተለየ ትኩረት የሚሰጥበት ሁኔታ የለም። የምርትና የንግድ ዘዴዎቹም በተቻለ መጠን በጥቂት ተቀጣሪዎች በመጠቀም ትርፍን ማካበት ነው። በዚህ ሁኔታ፣ በተለይም መጀመሪያ የካፒታሊስት ስርዓት በሚገነባበት ወቅት፤ ለከተማ ነዋሪው ሁሉ ሥራ የመፍጠር ፍላጎቱም ሆነ ብቃቱ አልነበረም። በተጨማሪም የሸቀጣ ሸቀጦች ዋጋ ገበር እስካለ ድረስ የድሃውን አቅም በማገናዘብ ዝቅ የሚሉበት ሁኔታ የለም። ስለሆነም በአውሮፓ በአስራ ዘጠነኛው መቶ ዓመት በገጠርም ሆነ በከተሞች የነበረው የድህነት ችግር የከፋ ነበር።

ድህነት፣ በአገራችን፤ ብዙ ዓይነት መልኮች አሉት። ድህነትን በሁለት መንገድ መገንዘብ ይቻላል። አንደኛው የአሃዛዊ-ስሌታዊ (statistical) ግንዛቤ ሲሆን፣ ይኸም በእውነት በኢትዮጵያ የሚታየው የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ድህነት ሁኔታ እጅግ ሰፊና አሳዛኝ መሆኑን ሁሉም የሚያውቀው ነው ወይም በቀላሉ ማሳወቅ የሚቻል ነው።[19]

ሁለተኛው በአሃዛዊ-ስሌት በቀላሉ ማሳየት የሚያዳግተው በግለሰብ ደረጃ ያለው የመንፈስ ድህነት ሆኖ በብዙ ሁኔታም ከመደበኛ ዓይነቱ ድህነት ጋር ይያያዛል። ይህም ቅንነት ማጣትን፣ በራስ ያለመተማመንና ለእራስ ጉዳይ እንኳን ከኃላፊነት መሸሽን እና

[19] የአለም ባንክ እና የተ/መ የልማት ፕሮግራም ዓመታዊ ዘገባዎች በየዓመቱ እያሽቆለቆልን እየሄድን በአሁኑ ወቅት ከመጨረሻ ሁለት ወይም ሶስት አገሮች ጋር መደመራችንን ያረዱናል። በተጨማሪም የአገራችን ዜጎች በቁጥት ግን በጥናታዊ መረጃ ተመርኩዘው ያቀረቡትን፣ Annual Report on the Ethiopian Economy, op. cit., ይመልከቱ።

ፍርሃትን ያካትታል። የዚህ ድህነት መንስዔ በየካቲቱ አብዮት ወቅት በመደብ ትግል ሰበብ በስፋት የተካሄደው አሰቃቂ ግድያ፣ አፈናና እስር አልባሌ ስቃይ ማድረስ አንደኛውና ዋነኛው ምክንያት ሲሆን፣ አሁንም በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ወቅት በየቦታው የሕዝብ እርስ በርስ መናቆርና ሲብስም መጋደል አላቆመም። የዚህ ችግር ክፋት በጥቅሉ ለማናቸውም ተግባር ያለው አሉታዊ አንድምታ ሆኖ ድህነትን ለመቅረፍ ለሚደረገው ጥረትም ሆነ የአጠቃላይ የልማት ሥራን በእጅጉ ሁለገብ በሆነ መንገድ አደናቃፊ ይሆናል ብዬ እገምታለሁ። በኅብረተሰቡም ውስጥ ለዚህ ያለው ግንዛቤ ደካማ ይመስላል። ይህ ችግር ከነመፍትሄው ትኩረት ተሰጥቶት ቢጠና ለአገራችን ሁለገብ ጥቅም እንደሚኖረው እርግጠኛ ነኝ። አንድ ስመ ጥር ፈላስፋ[20] የዘመናችንን አሰቃቂ ታሪክ–የሂትለርን 6 ሚሊዮን ይሁዳዎች መፍጀት፣ በየአብዮቱ እና በየጦርነቱ የተካሄዱትን ግድያዎች፣ ሩዋንዳ ውስጥ ሁቱዎቹ ቱትሲዎችን በሚሊዮን ይህ ነው ሊባል በማይችል ኢሰብአዊ ጭካኔ መጨረስ፣ ወዘተ፣ አጥንቶ ያገኘው ጨካኝ ገዳዮቹ ኅሳዊ ጥላቻና ጭፍን የአይዶሎጂ እምነት ያለቸው፣ እንዲሁም የግል ኃላፊነታቸው የተሸረሸረ ሆኖ ነው።

እዚህ ጽሑፍ ውስጥ የሚተኮረው በአሃዛዊ-ስሌት በትክክል መታወቅ የሚቻለው ድህነት ላይ ነው። ይህንን በሶስት ዓይነቶች ለይቶ ማየቱ ይጠቅማል።

1. አንደኛው ዓይነት እራሳቸውን ለመርዳት ምንም አቅም የሌላቸው በገጠርም ሆነ በከተማ የሚገኙት ናቸው። ይህ ጠዋሪ የሌላቸው ሽማግሌዎችና አሮጊቶችን፣ ቤተሰብ የሌላቸውን ህጻናት፣ ረዳት የሌላቸው አካለ ስንኩላንን ያካትታል። እነዚህ በገጠርና በተለያዩ የአገሪቱ ከተሞች የሚገኙት፣ ብዙውን ጊዜ በልመና የሚኖሩትና ጹር የሚያድሩት፣ ቁጥር አይታወቅም።

2. ሁለተኛው መሬት አጡ በገጠር ያለው ድሃ ገበሬ ነው። የዚህ ክፍል ችግር እላይ እንደተጠቀሰው በካፒታሊስት ስርዓት የነጋዴ ሰፋፊ በገበያ ለይ ያተኮሩ እርሻዎች አጣበው መሬቱን ያጣ ብቻ አይደለም። እንዲያውም ይሄ የወደፊት ችግር ነው

---

[20] Gonathan Glover, Humanity: AMoral History of the Twentieth Century. New Haven: Yale University Press, 2000.

እነጂ, ለአሁኑ ዋነኛው ችግሮች፣ እንደ አቶ ደሳለኝ[21]፣ በኢትዮጵያ የመሬትንና የገበሬውን ችግር እንደኚህ ምሁር የሚያውቁ በጣም ጥቂት ናቸው፣ አባባል ሁለት ናቸው፡፡ ሀ. የመሬት ባለቤትነት ስጋት፣ ለ. ያላቸው መሬት በየጊዜው በሚደረገው መከፋፈል ምክንያት መበጣጠስና ማነስ ነው፡፡ ከነዚህ ምክንያቶች በተጨማሪ በነዚሁ መንስዔ በአካባቢው ላይ የሚደርሰው ጉዳትና የመሬቱ መበላሸት፣ በየዓመቱ የሚያሽቆለቁለው የምግብ የማምረት መጠን፣ የሕዝብ ቁጥር በየዓመቱ የሚጨምረው፣ እና ሌሎችም በግብርናው መስክ ያሉ ድክመቶች፣ ድሃውን ገበሬ በቀጣይ መልኩ ለረሃብና ለችግር ይዳርጉታል፡፡ መንግሥት ካቀረበው ሰነድ እንኳን መረዳት የምንችለው 28 ሚሊዮን ገበሬ የምግብ ችግር አለበት፡፡ በአለፉት አምስት ዓመታት መንግሥት ከአራት እስከ ስምንት ሚሊዮን ለሚደርሱ ዜጎቹ የምግብ እርዳታ ከውጭ ለጋሾች በይፋ ሲለምን ነበር፡፡

3. ሶስተኛ የከተማውን ሥራ አጥ ይመለከታል፡፡ የከተማ ነዋሪው ሕዝብ በዓመት በግምት በስድስት በመቶ እያደገ ነው፡፡ በተጨማሪም የሕዝብ ቁጥር በሶስት በመቶ ገደማ ማደጉ ከተማውንም ይጫነዋል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪን ብዛት ማንኛውም ሰው በየትኛውም አቅጣጫ ቢዘዋወር በቀላሉ የሚታይ ነው፡፡

መልካም አስተዳደርና የኢኮኖሚ ልማት ድህነትን ከመቀነስ ጋር ያላቸው ግንኙነት የተለያየ ነው፡፡ በጥቅሉና በቀጥታ ማንኛውም አይነት የኢኮኖሚ ልማት፣ አዳዲስ የሥራ መስኮች በመክፈትና በሰፊት የሚሰራጭ ሀብት በመፍጠር፣ የድህነትን ችግር ይቀርፋል፡፡[22] ይህ በራሱ ትልቅ ውጤት ሆኖ ነገር ግን የካፒታሊስት ስርዓቱና

---

[21] የተለያዩ ብዙ ጥናቶች አቅርበዋል፡፡ እዚህ በዙ ቦታ ላይ የምላቸው ሃሳቦች ጊዜያዊውን የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ PRSPን አስመልክቶ በአጭሩ በሰጡት አስተያየት ላይ የተመረከዘ ነው፡፡ See Dessalegn Rahmeto, "Some Comments on the Ethiopian Government's Interim Poverty Reduction Strategy Paper (IPRSP)," in MEDREK, op.cit. pp. 5-9.

[22] "In a study of over 100 countries and colonies there was found to be correlation between G.N.P. per capita and such other indicators of economic and social development as the percentage of the population in cities of over 20,000 (r=.71), the percentage of adults literate (.80), the proportion of the population enrolled in higher education (.58), the number of radios per 1000 population (.85), and the number of hospital beds per inhabitant (.77). These variables, along with others like the

ገበያው የሚፈጥራቸውን መዋቅራዊ የድህነት ሁኔታን–የገጠሩን ድሃና የከተማውን ሥራ አጥ መቆጣጠር የፖለቲካ ጥያቄ ነው::

ጉዳዩም በመሠረቱ የመብት ጥያቄ ነው:: አንደኛ መግቢያው ውስጥ እንደ ጠቀስኩት በአውሮፓ ታሪክ በመጀመሪያ የሕግ (ሲቪል) እና የፖለቲካ የዜግነት መብቶች ሲረጋገጡ የካፒታሊስት/የቡርዡዋ ስርዓት መሠረት ተጣለ:: ከዚያ በመቀጠል ይኸው ስርዓት የፈጠረውን የድህነት ማኅበራዊ ቀውስ ለመቋቋም በመጨረሻ በትግል የተገኘው ማኅበራዊ መብት ነው:: መብቱም ዜጎች ሁሉ የአገራቸው የኢኮኖሚ አቅም በሚችለው መጠን ባለው ስልጣኔ የመሳተፍና ስርተው የኑሮዋቸውን ደረጃ የማሻሻል መብት ነው:: ይህ ብቻም አይደለም፣ በአሁኑ ወቅት ያሉት የሰለጠኑ አገሮች መንግሥታት ለጡረተኞች፣ ለአካለ ስንኩላን፣ ቤተሰብ ለሌላቸው ህጻናትና በማናቸውም ምክንያት እራሳቸውን መቻል ለአቀታቸው ዜጎች የሚሆን የግብረ ሰናይ ዕቅድ ስርዓታቸው አለው:: ለዚህም ነው አንድ አንዴ እነዚህ መንግሥታት የግብረ ሰናይ መንግሥት በመባልም የሚታወቁት::

ሁለተኛ እላይ የመልካም አስተዳደር ገጽታ በተመለከተበት ቦታ በመጀመሪያ የተጠቀሰው ዓይነተኛ ጠባይ ዜጎችን *በእኩልነት* የመውሰድ ዝንባሌ ነው:: ዜጎች እኩል ናችሁ ተብለው በአንጻሩ አንዱ በልቶ ሲያድር ሌላው ጦሙን ሜዳ ላይ ሲቀር፣ የአንዱ ልጅ በመኪና ጠዋት ወደ ትምህርት ቤት ሲሄድ የሌላው ልጅ በረንዳ አድሮ ጠዋት ልመና ሲወጣ ቅራኔውና ማኅበራዊ ቀውሱ በግልጽ የሚታይ ይሆናል:: ስለዚህ የዚህ መብት ጥያቄ ታሪካዊ ግንዛቤና መረጃው በሕዝብ ዘንድ ስላለ፣ የኛም መንግሥት በሰላምና በፖለቲካ ተረጋግቶ ለመቆየት በአገሩ ውስጥ ቢያንስ በግልጽ የሚታየውን የድህነት ሁኔታ መቋቋም አለበት::

---

percentage of the labor force employed in agriculture, the percentage of wage and salary earners in the population, and other indices of health and mass communications, form a cluster that tends to vary according to the level of economic development." Bruce M. Russett, Trends in World Politics. New York: Macmillan, 1965, pp. 125-26.

## VI- የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ (PRSP) ዝግጅትና የሕዝብ ተሳትፎ

ይህ አገር አቀፍና ሁለገብ ዕቅድ መንግሥታችን ተገዶ የተቀበለው ስልት ነው:: ማስገደጃው መንገድ አንዱ እንደማንኛውም ድሃና፣ ላይ በቦታው እንደተገለጸውም፣ ጥገኛ አገር ያለብንን አለም አቀፍ የብድር እዳ መክፈል ስለማንችል እዳው የሚቀነስልን ይኸንን ስልት ከተቀብልን ብቻ በመሆኑ፣ ሁለተኛ በወቅቱም ለደካማ ባጀታችን መደጎሚያ ለምንፈልገው የውጭ ምንዛሪ ይኸንን ስልት ካልተገበርን ብድር ከማንም ማግኘት እንዳንችል ማድረግ ይችላሉ:: ይህ ስልት ለጋሽ አገሮችና እንዲሁም የነሱ አለም አቀፍ የኢኮኖሚ ተግባር ቀኝ እጅ የሆኑት አለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና አለም ባንክ የወጡትና በአስገዳጅ መልኩ በአለም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን ድሃ አገሮችን ለመቆጣጠር በአሁኑ ጊዜ የሚጠቀሙበት ዘዴ ነው::[23] ሕዝብም ከመጀመሪያው ያልመከረበት ብሔራዊ ሉአላዊነታችንን የሚጠናወት ስልት ነው::

ከዚህ በፊትም ከውጭ በዙ ለዕድገት ይረዳሉ ተብለው የቀረቡልን በቃላት ያሸበረቁ ብሚጋጩ ሃሳቦች ግን ተኳኩለው ቀርበው ወደንም ሆነ ሳንወድ የተቀበልናቸው መርሆች ነበሩ ለምሳሌ መሠረታዊ ፍላጎቶችን ማሟላት፣ መዋቅራዊ ማሻሻያ ፕሮግራም:: እነዚህና መሰሎቻቸው መርሆዎች አለመሥራት ብቻ ሳይሆን ብዙ ጊዜ ማኅበራዊ ቀውስ ፈጥረውና ለተጨማሪ የብድር እዳ ዳርገውን አልፈዋል:: በኔ ግምት ያሁኑ ስልትም በሙሉ ልብ የተሻለ ዕጣ ይገጥመዋል ለማለት የሚያስችል ተሞክሮም ሆነ አዲስ የተለወጠ የአለም ሁኔታ የለም::

ለዚህ ለአዲሱ ስልት ድጋፍ የሚሰጡ ወገኖች የሚያቀርቧቸው ሶስት መከራከሪያ ነጥቦች አሉ:: አንደኛው ለጋሽ አገሮችና እነዚህ አለም አቀፍ የብድር ተቋማት ለመጀመሪያ ጊዜ የብድር እዳችንን የመሰረዝ መንፈስ በቁም ነገር ይዘውታል የሚል ነው:: በመሠረቱ በአሁን ወቅት አንደኛ እጅግ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውና በኢኮኖሚ ውጥረት

---

[23] ይህ ሁኔታ በቀጥታ የኢህአዴግ አብዮታዊ ፕሮግራም "ተነጻጻሪ ነፃነት ያለው ኢኮኖሚ መገንባት" የሚለውን የፓርቲውን አላማ ይቃረናል:: <u>የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የልማት መስመሮችና ስትራቴጅዎች፤</u>(ለውይይት የቀረበ) አዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ኢንተርፕራይዝ፣ ነሐሴ 1992 ዓ.ም.

ውስጥ ያሉ አገሮች ወደፊትም ቢሆን እዳቸውን መክፈል መቻላቸው አጠራጣሪ ነው:: ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚሰረዝላቸውን እዳ አገሮቹ ድህነትን የመቅረፍ ተግባር ላይ ያውሉታል የሚል ሲሆን፤ ነገር ግን የነዚህ አገሮች መንግሥታት ይህንን ወደፊት በእርግጥ ለመፈጸማቸው ምንም ዋስትና የለም:: ሁለተኛ የስልቱ ባለቤት አገሮቹ ናቸው የሚል አባባል አለ:: ይኸም "ዶሮን ሲያታልሏት..." በቀር የትኛውም ስልቱን ያዘጋጀ አገር ከላይ ከተጠቀሰው ብድራችሁ ይሰረዝላችኋል እለበለዚያ...ከሚለው ዛቻ በሻገር ለፍቶና ያለውን የሰው ኃይል አቅምና ገንዘብ አፍሶ ያዘጋጀው ስልት ሥራ ላይ ለማዋል የአለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማቱን ባለሥልጣናት ይሁንታ በግድ ይፈልጋል:: ሶስተኛ የስልቱ ዝግጅት የሕዘቡና በጎብረተ ሰቡ ውስጥ ያሉት የሲቪል ማኀበረሰብ ተሳትፎ ይኖርበታል የሚል ነው:: እዚህም ላይ ሕዝቡ በተለይም ተጠቃሚ ይሆናል ተብሎ የሚገመተው ድሃና ደካማ ክፍል በምን አቅሙ እንደሚሳተፍ ወይም በምን መንገድ የተሳትፎ አቅሙን ማጎልበት እንደሚቻል ወደፊት የሚታይ ነው::

በአንጻሩ ይህ ሰፊ ስልት ከአገሩ ብሔራዊ የረጅምና የአጭር ጊዜ ዕቅድና የልማት ስልት ጋር መጣጣሙ የተረጋገጠ አይደለም:: እንዲያውም ይኸንን አዲስ ስልት የሚገፉት የአለም የገንዘብ ተቋማት ከራሳቸው ጥቅምና እምነት ጋር እንዳይጋጭ የሚረጋገጥ አንጻራዊ የአቅም ብልጫቸውን በመጠቀም ሂደቱን እንደሚቆጣጠሩት ከወዲሁ መገመት ይቻላል:: ለመሆኑ የእነዚህ ድሃ አገሮች ፓርላማዎችና የተለያዩ የአገሮቹ ሕዝባዊ ተቋማት የስልቱን ጽንሰ ሃሳብና ለመቀበል የተካሄደውን ድርድር መክረውበታል ወይ? ይህ ስልት ከአገሪቱ ከእሉና ወደፊት ሊፈጠሩ ከሚችሉ የተለያዩ ችግሮችና የመፍትሂ ቅደም ተከተሎች ጋር ቢጋጭ ምን ይደረጋል? ሊሎችም ጥያቄዎች ማንሳት ይቻላል::

ለማንኛውም የዚህን የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ (PRSP) ዝግጅት በተመለከተ እዚህ የሚቀርበው አስተያየት የስልቱን ጽንሰ ሃሳብና አወቃቀር የአለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና አለም ባንክ (IMF and the World Bank) ባቀረቡት መልኩ ይወሰናል::[24] ይህን

[24] At any rate, as Dr. Birhanu observed, I hope not tartly, "It is also the only game in town." Dr. Birhanu Nega, "The PRSP and the Ehanced HIPC Initiative: ABrief Discussion." in MEDREK, The Newsletter of the Forum for Social Studies, April 2001, p. 17.

ስል ማሽሚጠጥም ወይም ያልሆነ ጥርጣሬ (cynical) መንፈስ ውስጥ በመሆን የግብር ይውጣ ሥራ ለማቅረብ አይደለም:: ማንኛውም የምንፈልገው ለውጥ ዝም ብሎ በራሱ አይመጣም:: ለመልካም አስተዳደር ዴሞክራሲያዊ መንግሥት እስኪመጣልን ቁጭ ብሎ መጠበቁ እንደማያዋጣ ሁሉ ይኸም ስልት በተሻለ ሁኔታ እንዲካሄድ ያሉትን ችግሮችና ገደቦች አውቆ በተቻለ መጠን ተፈጻሚነቱና ውጤቱ የተሻለ እንዲሆን መታገሉ ተገቢ ነው:: ድህነትን ለመቅረፍ የሚደረገው ጥረት በእውነት በሕዝብና በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ታቅፎና ተደግፎ በመጠኑም ቢሆን ከተከናወነ ለመስተዳደሩ መሻሻል፣ ለኢኮኖሚ ልማት ጅምርና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመገንባት ጥሩ መነሻ ይሆን ይሆናል::

ነገር ግን ሁላችንም፣ ማለትም መንግሥትም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም፣ ብሔራዊ ልዕልናችን በመጠኑ እንደተሸረሸረ ተገንዝበን ከዚህ በላይ አድጎ ማንነታችንን እንዳይጠናወት ከወዲሁ መጠንቀቅ አለብን:: የዚህ አደጋ ጥገኝነትን አሳመልክቶ በሁለት ዓይነት መንገድ ሊንጸባረቅ ይችላል::

1. ይህ ሰፊና አገር አቀፍ የድህነት ቅነሳ ስልት፣ እንደ መዋቅራዊ ማሻሻያ ፕሮግራምና ሌሎቹም፣ ለበለጠ እዳና ቀውስ ጥገኝነት ውስጥ ጥሎን እንዳያልፍ:: የሚሰጡንን ብድር ተቀብለንና በስልቱም ዝግጅት ያለ የሌለንን የሰው ኃይልና ገንዘባችንን አፍሰን በደንብ ሳንጠቀምበት ካለፈ፣ አሁን ያለው መንግሥት ጥገኝነትን ካለፈው መንግሥት እንደወረሰ ሁሉ ለሚመጣው መንግሥት ያስተላልፈዋል እኛም እዳችንን ለሚመጣው ትውልድ እናስተላልፋለን::

2. ሁለተኛው ዓይነት አደጋ የዚህን ስልት ተጠቃሚ በቀጥታ ይመለከታል:: ስልቱ ከጅምሩ በጥንቃቄ ካልያዝነው ድሃ ለምንለው ላይ የሚታዩት ችግሮችን በመቅረፍ ተወስኖ እንዳይቀር ያሰጋል:: እስካሁን የእንደኛው አለም ኃያላን የሶስተኛን አለም አገሮች መንግሥታት ጥገኛና ተመጽዋች ማድረግ ችለዋል፣ አሁን ደሞ የዚህ የድህነት ቅነሳ ስልት በዘላቂነት ሰዉን በራሱ ላይ ቆሞ ድህነትን መወጣት ሳይሆን ተመጽዋች ካረግነው ኅብረተሰቡ በሞላ ለማኝ ሆነ ማለት ይሆናል::

መልካም አስተዳደር

ከዚህ ቀጥሎ ለሚቀርበው ትንተና በመንግሥት የቀረበውን *ጊዚያዊ የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ (PRSP)*፣ አዲስ አበባ፣ ሕዳር 2000፣ እንደመንደርደሪያ እጠቀምበታለሁ:: አላማው፣ ዋናው የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ (PRSP) በሚዘጋጅበት ወቅት ይረዳሉ ብዬ የምገምታቸውን ሃሳቦችና ተመክሮዎች ለማቅረብ ነው::

በመጀመሪያ ዋናው የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ (PRSP) በሚዘጋጅበት ወቅት የድሃውን ቁጥርና ሌሎችም የኑሮውን መረጃዎች በጥናት (survey) ማጠናቀር አማራጭ የሌለው ተግባር ነው:: መንግሥት በዚህ በኩል በቤተሰብ አጠቃላይ ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ጥናት እንደሚያደርግ ተገልጹዋል:: ይህም ጥናት የድሃውን ዓይነት ቢቻል እላይ ከቀረበው በበለጠ ለያይቶ በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ፣ እንዲሁም የከተማና የገጠሩን፣ ሁሉንም በእድሜና በጾታ ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል:: እንዲሁም የትምህርት ደረጃቸውን፣ ዝንባሌያቸውንና የሥራ ልምዳቸውን ማወቅ በተለይም ዘላቂ ገቢ የማያስገኝ ዕቅድ ለመቀየስ በጣም ይጠቅማል:: እዚህም የሚቀርቡትን ሃሳቦች ላይ የድህነት ዓይነቶችን ከፋፍለን በአየንበት መልኩ፣ መፍትሂዎቹም ለሁሉም አንድ ወጥ መሆን ስለማይችሉ፣ እያንዳንዱ ችግር በተናጥል ማየቱ ይሻላል::

## የድህነት ቅነሳ ስልት መንደርደሪያ ሃሳቦች

እዚህም የሚቀርቡትን ሃሳቦች ላይ የድህነት ዓይነቶችን ከፋፍለን በአየንበት መልኩ፣ መፍትሂዎቹም ለሁሉም አንድ ወጥ መሆን ስለማይችሉ፣ እያንዳንዱ ችግር በተናጥል ማየቱ ይሻላል::

የመጀመሪያውን ዓይነት ድህነት አስመልክቶ ዶ/ር ብርሃኑ[25] ከጥቂት ዓመታት በፊት ያቀረቡትን ሃሳብ ብንመለስበት ጥሩ ይመስለኛል:: በአጭሩ፣ እሳቸው የሚሉት በራሳችን አነሳሽነት እና በምርጫ በተደገፈ ውሳኔ ሁላችንም ከገቢያችን ላይ የተወሰነ በመቶ እንዲቀነስ:: እንደገናም እራሳችን የመረጥነው አንድ አካል ሕጋዊ በሆነ መንገድ ተመሥርቶ፣ የድሆቹን መረጃ ተስማሚ ዕቅድ አውጥቶና ድሆቹን አሰባስቦ፣ ገንዘቡንና የሚፈጥረውን የግብረ ሰናይ ድርጅት እንዲቆጣጠረው:: ከመንግሥት የሚጠበቀው

[25] ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ፣ ጦቢያ ጋዜጣ

እርዳታ የዚህ ተቋም ማንኛውም ዓይነት የገንዘብና የንብረት እንቅስቃሴ ከቀረጥ ነጻ እንዲሆን፣ አስፈላጊው በመንግሥት እጅ ያለ ቁሳቁስና መሬት በነጻ እንዲሰጥ፣ እንዲሁም ህመምተኞች መንግሥት ሆስፒታሎች ልጆቹም መንግሥት ትምህርት ቤቶች በነጻ መታከምና መማር እንዲችሉ ነው:: የዚህ ዓይነት ዕቅድ በየክልሉና በየከተሞች ውስጥ ከአዲሱ ስልት ጋር በተቀናጀ መልኩ የማይተገበርበት ምክንያት የለም:: ከዚህ ጥረት ሁለት ጠቃሚ ውጤቶች ሲፈልቁ ይታየኛል:: አንዱ የመንግሥትን ሸክም ማቃለል ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ የዜጎችን ነፃ ተሳትፎ ያዳብራል::

በአጠቃላይ ለሁለተኛው እና ለሶስተኛው ዓይነት ድህነት ዋናው መፍትሄ ሁለገብ ከሆነ የኢኮኖሚ ልማት ውጪ ዘላቂ መፍትሄ መስጠት አይቻልም:: አቶ ብርሃነ መዋ፣[26] የኢትዮጵያና የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤቶች ፕሬዜዳንት፣ እንዳሉትም ድህነት የሚቀነሰው ሀብትን በማካፈል ሳይሆን ሀብትን በማፍራት ነው:: በሳቸውም እምነት ይሄ በተግባር ተፈጻሚነት የሚኖረው የግሉ ኢኮኖሚ ሲያድግ ስለሆነ የግል ባለሃብቶችን እዚህ ስልት ውስጥ በቀጥታ ተሳታፊ ማድረግ ያስፈልጋል:: አቶ ተካልኝ ገዳሙ፣ የአቢሲኒያ ባንክ ሊቀ ምንበርና ዋና ሥራ አስኪያጅም ተመሳሳይ አስተያየትና ድህነትን ከአገራችን የማጥፋት ቅን የሆነ አላማ የሚደግፍ አቋም አላቸው::

የሁለተኛውን ዓይነት፣ ማለትም የድሃ ገበሬዎችን፣ ችግር በተመለከተ የመንግሥት መፍትሄ ሃሳብ የግብርናን ልማት ማእከል አድርጎ በሚካሄድ የኢንዱስትሪ ዕድገት ውስጥ የተጠቃለለ ነው:: አቶ ደሳለኝ ላይ በተጠቀሰው ጽሑፋቸው እንዳስገነዘቡት ይህ የመንግሥት ዕቅድ (ADLI) መዋቅራዊ ለውጥ ውስጡ አያሳይም:: በዚህም ምክንያት ገበሬውን ለተለመደው ኑሮ በቀጣይ መልኩ ይዳርገዋል:: የግብርናው ዘርፍ ታሪክ መሻሻልን ካለማሳየቱ በሻገር አሁን በአለበት የቆረቆዘ ሁኔታ የኢኮኖሚያችን እንቅስቃሴ ሞተር መሆን አይችልም:: አቶ ደሳለኝ እንዳሉትም ጊዚያዊ ስልቱ የተለየ የሥራ መስክ ፍለጋን እንደ አማራጭ አያስቀምጥም:: ሆኖም ግን ጊዚያዊ ሰነዱ እዚህ ስልት ውስጥ የሚካተቱ፣ መሬት ለሌለውና ለሚፈልግም ገበሬ አማራጭ የሥራ መስክ ይጠቅሳል::

---

[26] አዲስ አድማስ፣ ሳምንታዊ ጋዜጣ፣ ጳጉሜ 3 1993 ዓ. ም.
[27] Tekalign Gedamu, "Troubling Times for Ethiopia's Banks: A Personal View," 14 September 2001, Unpublished.

መልካም አስተዳደር

በኔ ግምት በተለይም ከመሠረተ ልማት ዕቅዶቹ ውስጥ የመንገድ፣ የኤሌክትሪክና የንጹህ ውሃ ማዳረስ ሥራ በአካባቢው ለሚገኙ ገበሬዎች አመቺ የሥራ አማራጭ እድል ይሆናሉ። ከዚሁ ስልት ዝግጅት ጋር አብረው መታየት ያለባቸው ሌሎች ሁለት ቁም ነገሮች፡- 1. የመሬት ስሪቱ መሻሻልና መቀየር ጉዳይ አብዛኛው ሰው የሚስማማበት ነው።

2. ሰፋፊ የንግድ እርሻዎች መቋቋም ሊታገዝ ይገባል፣ በተለይ በምግብ ዋስትና በኩል እራሳችንን እንቻል ካልን ይህን ማድረግ የግድ ነው።

የሶስተኛውን፣ የከተማ ሥራ አጡን፣ በሚመለከት የኢኮኖሚያችን ሁለገብ ከሆነ የኢንዱስትሪ ፋብሪካዎችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች እድገት ውጭ ዘላቂ የሆነ መፍትሄ የለም። ብዙ ሰዎች አቶ ብርሃነን ጨምሮ እንደሚሉት የኢኮኖሚያችን የልማት እንቅስቃሴ ሞተር መሆን ያለበት ግብርና ሳይሆን ኢንዱስትሪ ነው። በዚህ ዘርፍም ሁነኛ ቦታ ሊሰጠው የሚገባውም የግል ባለሃብቱ ነው። በተለይ መለስተኛ የሆኑ አምራች፣ አገልግሎት ሰጪና የንግድ ተቋማት አዳዲስ የሥራ ዕድል በመፍጠር በኩል ሁነኛ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። ለኛም አገር የዕድገት ደረጃ የአገር በቀል ባለሀብት ሊበዛ የሚችለው በመለስተኛ ኢንዱስትሪዎችና የንግድ ድርጅቶች ላይ ተመርኩዞ ብቻ ነው። ከከተማ ሥራ አጦች ውስጥ አነስተኛም ቢሆን ብዙ የተማሩ እንደሚገኙባቸው መገመት ይቻላል። ከነዚህም የመንግሥቱ ጊዚያዊ ሰነድ በጠቆማቸው ዘርፎች ውስጥ የተወሰኑትን ማሰማራት ይቻላል። ከተጠቆሙት ዘርፎች ውስጥ ለዚህ ተስማሚ የሚሆኑት፣ የትምህርትና የጤና አገልግሎት ማስፋፋት፣ ኤችአይቪ ኤድስን የመካላከል ፕሮጀክት እና የቴሌኮሙኒኬሽን ስርጭት ሥራ ናቸው። በተጨማሪ የከተማው የመሬት ይዞታ እንደገና ተቃኝቶ አመቺ የመሬት ስሪት ቢወጣ የቤት ግንባታና ተዛማጅ የሆኑ እንቅስቃሴዎችም ለብዙ ሥራ አጥ ድሃ የሥራ ዕድል ሊፈጥሩ ይችላሉ።

## የተሳትፎና የትብብር መዋቅር መንደርደሪያ ሃሳብ

ዋናው የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ (PRSP) በሚዘጋጅበት ሂደት ውስጥ ትብብሩ የሚሆነው በመንግሥት፣ ይህን ሃሳብ በጠነሰሱ ሁለቱ አለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማትና መንግሥታዊ ባልሆነው ማኅበረሰብ ማካከል ነው። ትብብሩም እንዲሰምር ልክ እዚህ

ባስቀመጥኩት መልኩ ሰስቱም አካላት ግንዛቤ ኖሯቸው ለአንድ አላማ እንደሚሠሩ ሁሉ በአደባባይ በመመካከርና ማናቸውንም መረጃ ያለ አንዳች ገደብ በመለዋወጥ መሆን አለበት:: በአደባባይ ያልኩበት ምክንያት ስልቱ ካቀረበው መንደርደሪያ ሃሳብ በመነሳት ነው:: ይኸውም በመጀመሪያ ሥራው ግልጽና ተጠያቂነት ያለበት መሆን ይገባል በመባሉ፣ ሁለተኛ የእያንዳንዱ ተግባር ሂደትና ውጤት መገምገም አለበት በመባሉ ነው::

ከመንግሥትና መንግሥታዊ ካልሆነው ማኅበረሰብ የተውጣጣ አገራዊ የሆነ ወይም በፌድራል ደረጃ የሚንቀሳቀስ አንድ ግብረ ኃይል መቋቋም አለበት:: ይህ ግብረ ኃይል ማሰባሰብ ያለበት አራት የኅብረተሰቡ ዋና ዋና አካላት ይታዩኛል::

1. አንደኛ መንግሥት ነው:: መንግሥት ከወዲሁ እንደተዘጋጀ የሚያሳየው ቀደም ብሎ ጊዜያዊ የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ (PRSP) ማዘጋጀቱ ነው::

2. መንግሥታዊ ካልሆነው የሲቪል ኅብረተሰብ ተወካዮች የራሱ የሆነ ኮሚቴ ሊኖረው ይገባል፣ እዚህም ኮሚቴ ውስጥ በአባልነት ተካፋይ የሚሆኑት የሚከተሉት ድርጅቶች ተወካዮች ቢሆኑ ይጠቅማል::
    - የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ወኪል፣
    - የኢትዮጵያ የእስልምና ሃይማኖት ጉባዔ ወኪል፣
    - የሠራተኞች ማኅበር ወኪል፣
    - የገበሬዎች ማኅበር ወኪል፣
    - የመምህራን ማኅበር ወኪል፣
    - የሴቶች ማኅበር ወኪል፣
    - የወጣቶች ማኅበር ወኪል፣
    - የጋዜጠኞች ማኅበር ወኪል፣
    - የአራት ወኪሎች ከሌሎች የሙያ ማኅበራት::

3. የግሉ ኢኮኖሚ ወኪሎች በንግድና አምራች ማኅበሮቻቸው አማካይነት።

4. መንግሥታዊ ያልሆኑ ድረጅቶች (NGOs)፣ እነዚህ ድረጅቶች በ«የክርስቲያን በጎ አድራጎትና የልማት ድርጅት» ሰብሳቢነት ጥሩ ጅምር ያደረጉ ይመስላል።

ነገር ግን እስካሁን እንደሚታየኝ የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ ዝግጅት ሥራ ውስጥ መንቀሳቀስ የጀመሩት አካሂዳቸው ለየብቻ ነው። ይሄ አያያዝ የተለያዩ ተግባሮችን በመደጋገመና ባለመደጋገፍ የአቅም መባከንን ያስከትላል። መንግሥትም ያለው አይታ እዚህ የተጠቀሱትን አካላትም ሆነ ሌሎችን ማማከር (consultative approach) እንጂ ማሳተፍ መንገድን የያዘ ወይም የመረጠ (participatory approach) አይመስልም። እዚህ የቀረበው ተመክሮ፣ በሌሎች አገሮች በተለይም በኬንያ ልምድ ላይ ተመረከዘ፣ ተሳትፎ በይፋ በተዋቀረ መንገድ ቢሆን ይሻላል የሚል ነው። ምክንያቱ ግልጽ ነው፣ ውሱን የሆነውን የገንዘብና የሰው ኃይል እንዲሁም አስፈላጊውን ግብአቶች አሰባሰቦና አቀናጅቶ መጠቀም የበለጠ አመርቂ ውጤት ስለሚያመጣ። ይህ ግብረ ኃይል በፌደራል ደረጃ የራሱ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴና ጽሕፈት ቤት ሊኖረው ይገባል።

በሁለተኛ ደረጃ በየክልሎቹ እና በአዲስ አበባ ተጠሪነታቸው ለዚህ ኮሚቴ የሆነ መሰል ኮሚቴዎች ይቋቋማሉ። እንዲሁም አቅማቸው በፈቀደ መጠን በዞን፣ በወረዳ እና በቀበሌ ደረጃ አነስተኛ ኮሚቴዎች ይቋቋማሉ። ወደ ተጠቃሚው ድሃ ሕይወትጋ ለመድረስና እራሱን ለማሳተፍ እንዴት አድርጎ የሰው ባህል የፈጠራቸውንና የሚያውቃቸውን ማኅበራዊ ድርጅቶች ማሳተፍ እንደሚቻል ከአሁኑ መታሰብ አለበት። ለምሳሌ ያህል ለመጥቀስ እድር፣ የሃይማኖት ማኅበራት፣ ሰንበቴ፣ እቁብ፣ ወዘተ። ትልቁ ኮሚቴ አንድ ተነቃናቂ ግብረ ኃይል ፈጥሮ የነዚህን ኮሚቴዎች መቋቋም ተግባር ያግዛል። ከወዲሁ የዚህን መንግሥታዊ ያልሆነውን ማኅበረሰብ ተሳትፎ ለማረጋገጥ ቀደም ብለው ለዚህ ጉዳይ ትኩረት የሰጡት ድርጅቶች ኃላፊነቱን ወስደው የማኅበረሰቡን የማዋቀር ሥራ በቶሎ መጀመር አለባቸው።

መንግሥትም ለዋናው የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ (PRSP) ዝግጅት በተለይ የተመደበ የዚህን ዓይነት አስፈጻሚ አካል የሚመስል እንዲያውም በተሻለ መልኩ አዘጋጅቷል ወይም ያዘጋጃል ብዬ አምናለሁ:: ከዝግጅቱ የሥራ ሰቅድ ጀምሮ በሁለቱ መካከል የማያቋርጥ ትብብርና መመካከር መኖር ለውጤቱ ስኬታማነት አስፈላጊ ነው:: በአንድነት መሥራት ከተቻለም ጥሩ፣ ካልሆነ ግን የተቀናጀ የሥራና የኃላፊነት ክፍፍል ማድረግ ያስፈልጋል:: መንግሥታችንን አሁን የሚመራው ፓርቲ፣ ኢህአዴግ፣ ሁሌም በሰቅድ ደረጃ የተዘጋጀ ስለሚሆን፣ በዚህም ጉዳይ ላይ የተጻፈና የአለቀ ሰነድ ይዞ እየመጣ በምክክር ፈንታ አጽድቁልኝ ከማለት መቆጠብ ይኖርበታል:: ከአለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅትና አለም ባንክ (IMF and the World Bank) ባለ ስልጣኖች ጋር በሚኖረውም ውይይትና መደራደር በፌዴራል ምንግሥቱ ደረጃ ሆኖ የመንግሥታዊ ያለሆነው ማኅበረሰብ በትልቁ ኮሚቴ በኩል እኛን ወክሎ ይሳተፋል ብዬ እገምታለሁ::

ይህ ስልት እንዲሳካ የሁላችንንም እመኔታና ተሳትፎ ይጠይቃል:: ስለሆነም ከአለም አቅፍ አበዳሪ ድርጅቶቹም ሆነ ከኛ መንግሥት በኩል ግልጽ መሆን ያስፈልጋል፣ ስልቱን የሚመለከቱ መረጃዎች ሁሉ ለሕዝቡ በይፋ መታወቅ አለባቸው:: አሁን ባለው ደረጃ ስለዚህ የሁሉንም ሕይወት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንግድ የሚነካ ስልት ዝግጅት ከሚያውቀው ሰው የማያውቀው እንደሚበዛ ጥርጣሬ የለኝም:: ከወዲሁ በመንግሥት በኩል ሳይውል ሳያድር መደረግ ያለባቸው የማስታወቂያ ተግባሮች አሉ:: አንደኛ ጊዚያዊው የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ (PRSP) በአማርኛና ከተቻለም በዋና ዋና ቋንቋዎቻችን ተተርጉሞ መታተም ይኖርበታል፣ ህተመቶቹም ለሚያስፈልገው ሁሉ እንዲዳረስ መደረግ አለበት:: ሁለተኛ ይህ ስልትና ስልቱን አስመልክቶ እስካሁን ከአለም አቀፍ አበዳሪ ድርጅቶቹ ጋር የተደረገው ድርድርና የተደረሰው ስምምነት በመንግሥት መገናኛ ብዙሃንና በግል ጋዜጦችም ዜናው ለሕዝብ እንዲደርስ መደረግ አለበት::

## የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ (PRSP) ዝግጅትን በተመለከተ

የስልቱን ዝግጅት ለማስፈጸም በአሁኑ ወቅት የተለያዩ የቴክኒክ ኮሚቴዎች እንደቋቋሚል ሲባል ይደመጣል:: የነዚህ ኮሚቴዎች ሚናም ምን እንደሆነ ለጊዜው አይታወቅም:: በማንኛውም መንገድ ሕዝቡ እዚህ ተግባር ውስጥ ይሳተፋል እንዲያውም የሕዝቡ መሳተፍ እንደ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ይታያል ከተባለ መንግሥት ከአሁኑ የሚዋቀረው አስፈጻሚ አካል እንዴት አድርጎ መንግሥታዊ ከአልሆነው አካል ጋር አብሮ እንደሚሠራ መተለም አለበት:: የሚሻለውማ ከአሁኑ ሁለቱም ክፍሎች የሚተባበሩበትን ዘዴና መንገድ አብረው ቢቀይሱት ነበር:: በማናችውም መንገድ ስልቱ አገሪቱን በሙሉ ስለሚነካ ላይ መንግሥታዊ ለአልሆነው አካል እንደተመከረው አሁን በሥራ ላይ ያለውን የአገሪቱን የአስተዳደርና የኃላፊነት አወቃቀር መከተል የግድ ይመስለኛል:: በአማራጩ መንግሥት በእንደዚህ መንገድ ነው ልሠራ ያሰብኩት ካለና መንገዱም ጋሬጣ የማይበዛው ከሆነ ሕዝቡ ተቀብሎ የራሱን የትብብር አደረጃጀት በማስተካከል ሊያጣጥም ይችላል::

ገና ከጅምሩ ችግር እንዳይፈጠር ይኸን ተግባር መንግሥት ለሕዝቡ በቶሎ ማስታወቅ አለበት:: ከዚህ ጋር የሚዛመደው ሌላው ተፈላጊ ጉዳይ መንግሥት ለሚወስነውና ለሚወስደው እርምጃ፣ ከዚህ በፊት እንደተባለው፣ የሕዝብን እመኔታ ማግኘት ይኖርበታል:: ይኸም ብቻ አይደለም:: የዚህን ስልት ዝግጅት የተሳካ ለማድረግ ብሎም የአለም አቀፍ አበዳሪዎቹን ይሁንታ ለማግኘት መንግሥት የሕዝብ ትብብር ያስፈልገዋል:: ትብብሩ በቀላሉና በጸጋ የሚመጣው ሕዝቡ ይኸን ስልት ከተስማማበት ነው:: በስልቱ ላይ ደሞ ስምምነት (consensus) እንዲኖር የስልቱን ጥቅምና ጉዳቱን ለሕዝብ በዝርዝር ማሳወቅና ማስረዳት ያስፈልጋል፣ ቢያንስ ለከሂሎቹ::

ከወዲሁ የስልቱን ዝግጅት አስፈጻሚ አካላት ማወቅና ስልቱንም ለነሱ ማሳወቅ ሌሎች ተዛማጅ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን ሳይዘገይ ለመውሰድ ይረዳል:: እነዚህም መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች ለአስፈጻሚው አካል ተግባር ስኬታማነት አስፈላጊ የሆኑ አራት ጠባዮችን ያመለክታል::

1. እነዚህ አካላት የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ (PRSP) ዝግጅት ተግባርን አመርቂ በሆነ መልኩ ለመፈጸም ያላቸው ፍላጎትና ቀናኢነት (commitment) ምን ያህል ነው? ለዚህ እያንዳንዱ ተሳታፊ በግልና የተለያዩ ድርጅቶችም የስልቱን ምንነትና አላማውን በማያሻማ መንገድ ማወቅ አለባቸው:: አስፈላጊ ከሆነም ተገቢው ቅስቀሳ መደረግ ይኖርበታል::

2. አካላቱ ስልቱን በተግባር የመፈጸም አቅማቸው ምን ያህል ነው? አቅማቸው በቂ ሆኖ ከአልተገኘ የሚያስፈልጋቸው የስልጠናም ሆነ የገንዘብና የቁሳቁስ ድጎማ ወይም የሙያተኛ የሰው ኃይል እገዛ ማድረግ ያስፈልጋል:: አካላቱ የአሠራርና የአመለካከት ለውጥ ያስፈልጋቸው ይሆናል:: ከዚህ በታች ለስልቱ መሳካት ትልቅ ድርሻ ይኖራቸዋል ብዬ ለገመትኳቸው ሶስት የኛ መንግሥት ተቋሞች ላይ አስተያየት አቀርባለሁ:: እነሱም የቢሮው ስርዓት፣ የቀበሌዎች ሁኔታና የፌዴራል አወቃቀሩ ናቸው::

3. ብዙውን ጊዜ እነዚህ አስፈጻሚ አካላት በየመስካቸው የነበራቸውን ኃላፊነትና የሥራ ድርሻ እንደያዙ ነው እዚህ ስልት ዝግጅት ውስጥ የሚሳተፉት:: በወቅቱ ያላቸውን ሥራና ኃላፊነት የማሸጋሸግ ችሎታውና ዕድሉ አለ ወይ?

4. ተሳትፎን በተመለከተ እነዚህ የመንግሥት አካላት ከተቀረው ሕዝብ ጋር መሥራት መቻል አለባቸው:: ከወዲሁ በስልቱ ዝግጅት ውስጥ ሚና የሚኖራቸው መንግሥታዊና ያልሆኑት ተዋውቀው በትብብርና በስምምነት አብረው ለመሥራት ዘዴና መንገድ መቀየስ ያስፈልጋል:: ከዚህ በፊት መንግሥታችን በሰላም ጊዜ የሲቪል ማኅበረሰቡን በፍቃዱና በስምምነት ያሳተፈበት ተሞክሮ ብዙ የለም::

በኔ ግምት የቢሮው ስርዓትና ቀበሌዎች ለስልቱ ዝግጅት ትልቅ የሥራ ድርሻ ይኖራቸዋል:: የቢሮ ስርዓቱን በተመለከተ ብዙ ሰው ሲያጉረመርም ይደመጣል:: አንዱ ከአሜሪካ እዚህ ድረስ በራሴ ወጭ መጥቼ በብዙ መቶ ሺህ ዶላር ኩባንያ ለማቋቋም ብጥር ቢሮክራሲው አላሠራ ስላለኝ መመለሴ ነው ሲል ሌላዋ ይኸው ሁሉን ነገር ካሟላሁ በኋላ ፊራሚ አጥቼ ስንገላታ ሳምንት ሆነኝ እያሉ በቢሮክራሲው የሚያማርሩ

ብዙ ናቸው:: እንደ እውነቱ ግን ይሄ አባባል በፍጹም ትክክል አይደለም:: ቢሮው አንድ የማይናገር የማይላወስ በድንጋይ ወይም በእንጨት የተገነባ ህንጻ ነው:: ሰዉን የሚያሸማቅቀው ስም ያለው ያውም የቢሮ ስልጣኑን ከሚገልጽ የሹመት ቅጽል ጋር አንድ ሌላ ሰው ነው:: ችግሩ የለም ለማለት ሳይሆን ችግሩን የሚፈጥሩት ሰዎች፣ ያውም እኛ በከፈልነው ግብር ጥሩ ደሞዝ እየተከፈላቸው የሚኖሩት፣ እና እነሱን እዚያ ቦታ ላይ ያስቀመጠው መንግሥት ነው::

እንዲያውም የቢሮክራሲ አደረጃጀት የሰለጠኑትን አገሮች ዓይነተኛ ጠባይ ከሚያንጸባርቁት ከዋናዎቹ አንዱ ነው::[28] ታላቁ የጀርመን ሊቅ ማክስ ዌበር እደተነተነው፣ ለዘመናዊው የሰለጠነ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ኑሮ ከዋነኛዎቹ አንዱ ምክንያት የቢሮ ስርዓት ነው:: ሥራው በግልጽነት (transparent) እስከ ተገበረ ድረስ፣ የሥራ ክፍፍሉ የድርጅቱን አላማ እስከተከተለ ድረስ፣ የሥልጣን ሰንሰለቱ በሕጋዊ ደንብ ላይ እስከ ተመሠረተ ድረስ እና የቢሮው ባልደረቦች ለኃላፊነታቸው ተጠያቂ (accountable) እስከሆኑ ድረስ፣ እንደ የቢሮ ስርዓት በተቀናጀ መንገድ ግብን ለመምታት አመቺ የሆነ አማራጭ መሣሪያ የለም:: እኛማ በእውነት ከአንድ ሃያ ሰባት ዓመት በፊት ከአንደኛው አለም አገሮች የቢሮ ስርዓት ጋር የሚወዳደሩ እንደ ዩኒቨርሲቲው፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ መብራት ኃይል የመሰሉ ድርጅቶች ነበሩን:: ትዝታው ካለን ተስፋ መቁረጥ የለብንም::[29] የኛም መንግሥት ይህንኑ በመገንዘብ ለማንኛውም አገራዊ ተግባር እንቅፋት እንዳይሆን የቢሮውን ስርዓት ማሻሻል አለበት::

ያለፈው የወታደር ጁንታ መንግሥት ሕዝቡን ለመቆጣጠር እንዲያመቸው የተለያዩ ማኅበራት በየምክንያቱ እንዲመሠረቱ አድርጓል:: ከነዚህም በአገራችን በየቦታው

---

[28] Talcot Parsons identifies the differentiation of a comlex of structures whose 'universal development' is a necessary condition for 'higher lelel of adaptive capacity And they are money and markets, democratic forms of political association, bureaucratic organizations and universalistic legal system. See his The System of Modern Societies. Englewood Cliffs: Prentice-Hall, 1971, specially the chapter on "Evolutionary Universal in Society."

[29] Bahru Zewde, "The Problems of Institutionalization in Modern Ethiopia," in Proceedings of the Ninth Annual Conference on the Ethiopian Economy, op. cit. 13-23. ፕሮፌሰር ባህሩ ለዚህ የሚሰጡት ዋናው ምክንያት በወቅቱ የቢሮ ስርዓቱ ከመንግሥት ባልቃ ገብነት የነበረውን አንጻራዊ ነጻነት ነው::

ተንሰራፍቶ የሚገኘው አንዱ የቀበሌ ማኅበር ነው:: የቀበሌ ማኅበራት በወቅቱ እንደ ፖሊስ ጣቢያ፣ እስር ቤት ያውም ስቃይ ማሳየትና ግድያ የሚካሄድባቸው፣ ለነዋሪው ሰው አገልግሎት በዘፈቀደ ሰጪ፣ ለመንግሥት ድጋፍ ነዋሪውን በግድ አሰላፊ፣ ሆነው አገልግለዋል:: አሁንም፣ አንዳንድ አስከፊ ሥራቸው የቀነሰ ቢሆንም፣ ብዙ ከዚያን ጊዜ ተሞክሯቸው የቀሩ ልምዶች አላቸው:: እራሳቸውን የሚያዩት እንደ ፈላጭ ቆራጭ የመንግሥት አካል እንጂ ለነዋሪው ሰው አገልግሎት ሰጪና የሚከፈላቸውም ደሞወዝ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከነዋሪው እንደሆነ አይገነዘቡም:: ማንኛውም የነዋሪነት ማረጋገጫ ደብዳቤ ከቀበሌው የፈለገ ሰው ሁሉ ችግሩን ያውቀዋል:: መንግሥት በጥቅሉ የሚለው ለነሱ የዝመት ትእዛዝ ነው፣ መንግሥት የጠላውን ይጠላሉ የወደደውን ይፈራሉ:: ለስልቱ ዝግጅት ስኬታማነትም ሆነ ለማንኛውም ተግባራቸው መሻሻል ሁለት ነገሮች መደረግ አለበት::

1. በመጀመሪያ ተጠሪነታቸው ለነዋሪው ሰው እና ለሕግ እንደሆነ በማያወላውል መንገድ ማሳወቅ፣
2. ሁለተኛ በማንኛውም የቀበሌ ስልጣን ደረጃ ያለ ግለሰብ አጥፍቶ ሲገኝ በአፋጣኝ የሚቀጣበት ሁነኛ ዘዴ እንዲፈጠር ያስፈልጋል::

አሁን ያለው የፌዴራል አወቃቀር በሁለት በኩል የዚህን ስልት ዝግጅት ሊያዳክመው እንድያውም ከናአካቴው ሙሉ በሙሉ ፕሮግራሙን ሊያፈርሰው ይችላል:: አንደኛ በጎሳ ላይ ስለተመሠረተ ለሥራ ተፈላጊ የሆኑትን ባለሙያዎችም ሆነ ወይም ድሃ ዜጎች ከክልላቸው ውጪ ከድህነት የሚያወጣ የሥራ ዕድል ቢገኝ እንደ አስፈላጊነቱ ከቦታ ቦታ ማዛወር በቀላሉ አይቻልም:: ይሄ ሰው ወይም ያች ሴት ከኔ ጎሳ ወይም ክልል ስላልሆነ/ች አትምጣብኝ ወይም አይሂድብኝም ማለት የየክልሉ ፈንታ ነው:: ሁለተኛ፣ ዶ/ር ሳሙዔል አሰፋ እንዳስገነዘቡት፣ በተለይ የመገንጠሉ መብት የፌዴራሉን መንግሥት ልዕልና በእርግጥ በሕገ መንግስታዊ መንገድ ይገድበዋል:: የፌዴራሉ ፖሊሲ በማንኛውም ክልል ውስጥ ተፈጻሚነቱ በክልሉ ፍላጎት ነው፣ በተለይም የተቃወመው የክልል መንግሥት እንጻራዊ የጎለበት አቅም ካለው:: ይሄም ማለት ይኸንን የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ (PRSP) አንዱ ክልል በአጥጋቢ ምክንያት አልቀበልም ቢል በፌዴራሉ

ደረጃ የዚህ ስልት ተቀባይነትም አጠራጣሪ ይሆናል::[30] ይሄ እንዳይሆን መንግሥት ከወዲሁ ከየክልሎቹ የይሁንታ ስምምነት ማግኘት ያስፈልገዋል::

## የዚህ ስልት ዝግጅትና የዴሞክራሲ ግንባታ

የአለፈው አስር የስልጣን ዘመኑን ሲገመግም ኢህአዴግ ባለፉት ስባት ወራት ገደማ አገሪቱን በእንጥልጥል አቆያት:: ሕዝቡም በዚሁ ምክንያት የተፈጠረውን የኢኮኖሚውንና የማኅበራዊውን ቀውስ ችሎ እንዲሁም የፖለቲካ አለመረጋጋቱና ሰላም ማጣቱ ሳያስበረግገው እዚህ ደርሰናል:: ይኸም በአንድ በኩይ ጠንካራ ኅብረተሰብ ለመሆናችን ምስክር ነው:: ኢህአዴግም አንድ አንድ በግምገማው ሂደት የጠቀሳቸው ጥፋቶች ሰዉ በወቅቱ ሲላቸው የነበሩ ስለሆነ በእውነት "ተሃድሶ" በአዲስ የሰላም መንፈስ መጥቶ ከሆን እሰዬው ነው:: የዚህ የድህነት ቅነሳ ስልት ሰነድ (PRSP) ዝግጅት ቢያንስ የተሃድሰውን አቅጣጫ በተግባር ለማየት በወራት በሚቆጠሩ የጊዜ ገደብ እንችላለን::

የኢህአዴግ አንድ ዓይነተኛ ጉድለት የሚመስለኝ ከሕዝብ መራራቁ ነው:: ከሕዝቡ ተቀራርቦ በሰላምና በስምምነት ተጋግዞ አገርን ለመገንባት ኢህአዴግ ባለፉት አስር ዓመታት ብዙ ዕድል አጋጥሞታል:: የመጀመሪያው ገና ሲገባ የሰዉ አቀባበልና ተስፋ፣ ሁለተኛ በሽግግሩ ዘመንና የሕገ መንግሥት ማጽደቅ ወቅት፣ ሶስተኛ ሁለቱ የፌዴራል የፖለቲካ ምርጫ የተካሄዱባቸው ወቅቶች፣ አራተኛ ከኤርትራ ጋር ጦርነት በነበረበት ወቅት የነበረው የትብብርና የብሔራዊ ስሜት ወቅት፣ ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው:: አሁን አምስተኛ ዕድል ገጥሞታል:: ይኸውም በአንድ በኩል ፓርቲውና መሪዎቹ ተሃድሶ አካሂደን ተራርመን ታርመን መጣን እያሉ ነው፣ በሁለተኛ በኩል ይህን ሁለገብ ስልት ከሕዝቡ ጋር በመተባበር ለማዘጋጀት ለኃያላን አለም አቀፍ ተቋማት ቃል ገብቷል::

---

[30] ጽሑፉ ባለፈው ዓመት ተካሂዶ በነበረው የሕዋሃት መቋቋም 25ኛ ዓመት በዓል ላይ በተደረገ ስብሰባ ዶ/ር ሳሙኤል "የልዕልና ሁለት ጽንሰ ሃሳቦች" በሚል ርእስ ያቀረበው ነው:: It was reprinted in Addis Tribune, Friday, March 24, 2000, p. 6.

በአጽንኦት ለማለት የምፈልገው፣ የዚህን ስልት ዝግጅት አስመልክቶ፣ በቅርብ ጊዜ የኢህአዴግን የዴሞክራሲ ግንባታ ተስፋ ሀቅ ላይ መመሥረቱን ከሚቀጥሉት ተጨባጭ ተግባራት መገንዘብ እንችላለን::

1. የዴሞክራሲ ግንባታ ሂደት የሕዝብን እምኔታ ይጠይቃል:: በሚቀጥሉት ጥቂት ወራት ውስጥ የኢህአዴግ መንግሥት ለዚህ ስልት ዝግጅት ከሕዝቡ ጋር የሚሠራበትን ዘዴ ያስታውቀናል:: በዚህም ለሕዝቡ ያለው አመለካከት መሻሻሉን ማየት እንችላለን::

2. የዴሞክራሲ ግንባታ ተግባር የሕግ ልዕልና መከበር ያስፈልገዋል:: የቢሮ ስርዓቱ መሻሻል እና የቀበሌዎችን ተግባር በሕግ መወሰኑ፣ እንዲሁም ሁለቱም ከሙስና የጸዱ መሆናቸው ለስልቱ ዝግጅት አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታ ናቸው:: ይኸም መደረግ ያለበት ሕግና የሕግን ስነ ስርዓት ተመርኩዞ ነው:: የዚህም አፈጻጸም የፓርቲውን ዴሞክራሲያዊ ዝንባሌ ያሰየናል::

3. የዴሞክራሲ ግንባታ አላማ ከአንድ ፓርቲ ጥቅም ከአስፈለገም ህልውና ይበልጣል:: ለስልቱ ዝግጅትም ሆነ የቢሮ ስርዓቱን ለማደስ ኢህአዴግ ብዙ የፓርቲው ካድሬ ያልሆኑ ነገር ግን በሙያና በልምድ ብቃት ያላቸውን ዜጎች መቅጠር ይኖርበታል:: ይኸን ካረገ ፓርቲውንና መንግሥትን ለይቶ ማየት ችሏል ማለት ነው::

4. የዴሞክራሲ ግንባታ ተግባርን ነፃ ገበያና የባለንብረትነትን መብት መከበር ይደግፈዋል:: የኢኮኖሚውን ልማት በተመለከተ ለስልቱ ዝግጅት መስካት የገጠርና የከተማ የመሬት ስሪት እንደገና መቃኘት ይኖርበታል:: ይኸም በሥራ ላይ ሲውል ካየን ኢህአዴግ በእርግጥ ወደ ዴሞክራሲያዊ አመለካከት ፊቱን ዞር አርጓል በተጨማሪም የሕዝቡን አስተያየትና ፍላጎት እግምት ውስጥ ማግባት ጀምሯል ማለት ነው::